# ትንሣኤ



እግዚአብሔር በአካል ሦስት ፤ በመለኮት አንድ እንደሆነ እናምናለን ።

ቁጥር 40 ጥር ፲፱፻፸፫ ዓ.ም.



የጥምቀት በዓል አከባበር ሥነ ሥርዓት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ·

www.ethiopianorthodox.org

“ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረ ጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ “ትንሣኤ” ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ
ም/አዘጋጅ ራዱ አስረስ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

# ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| እንዲት ጥምቀት | ፪ |
| ትምህርተ ሥላሴ | ፫ |
| ታቦትና ክብሩ | ፮ |
| ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት | ፰ |
| ጥምቀት በብሉይና በሐዲስ ኪዳን | ፱ |
| ክርስቲያናዊ ጋብቻ | ፲ |
| ምሥጢረ ቁርባን | ፲፫ |
| ይህን ያውቁ ኖሯል? | ፲፬ |
| የተፈጥሮ ሕግና የተአምር ለውጥ | ፲፮ |
| ልማት በቤተ ክርስቲያን | ፲፯ |
| ሊቃውንቶቻችን | ፲፰ |
| የምእመናን ድምፅ | ፳ |
| አማን በአማን | ፳፩ |
| መልካም ዜና ለአብያተ ክርስቲያን | ፳፬ |


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አ.አ.

እምነት ያለ ምግባር ምግባርም ያለ እምነት እንደማያድን በያዕቆብ መልእክት 2 ፡ 14 - 26 ተገልጦአል ። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች በምግባር አንድ ንም ምክንያቱም “ሕጉን መፈጸም ስለማንችል ራሱ ጌታችን ፈጽሞልናል” ይላሉ ። ከዚህም ሌላ በእምነትና በምግባር እንጸድቃለን የሚሉትን ሲነቅፉ እየሰማሁ እጅግ አዝናለሁ ። ስለዚህ ትክክለኛውን ሃሳብ እንድታብራሩልኝ እጠይቃለሁ ።

የመጽሔታችሁ ተከታታይ
ወ ት ቀለሟ ነገደ
ከፍተኛ 5 ቀበሌ 21
አዲስ አበባ

● ወይዘሪት ቀለሟ ስለ ጥያቄሽ እናመሰግናለን ። እምነትና ምግባር የማይለያዩ ናቸው።ምግባር የእምነት ውጤት ወይም ፍሬ ነው ። አንድ ሰው በእርግጥ እውነተኛ እምነት ካለው እምነቱ ግድ ምግባር ያሠራዋል ። ምግባር የማይሠራ ደግሞ እምነት እንዳለው ያጠራጥራል ። ምግባር ያላቸውንም ሰዎች መንቀፍ አይቻልም ። ክርስቲያን ሌሎችን መንቀፍና በሌሎች መፍረድ አይገባውምና ። በጠቅላላ እምነትና ምግባር እንደቅጠልና ፍሬ እንደ ቀዋሚ አካልና ጥላ እንደ መሠረትና ሕንጻ ናቸው ። ግን ከቅጠል ፍሬ ከጥላ ቀዋሚ አካል ከሕንጻ መሠረት እንደሚቀድም ከምግባርም እምነት ይቀድማል ። ይሁን እንጂ መሠረት ያለ ሕንጻ ሕንጻም ያለ መሠረት ዋጋ እንደሌለው ሁሉ እምነት ያለ ምግባር ምግባርም ያለ እምነት እንደማያድን አንች ራስሽ የጠቀስሽው መልእክት ያስረዳል ።

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ በጌታ ስም ሰላምታ አቀርባለሁ ጥያቄዬ ስለ ቤተ መጻሕፍቱ ችግር ነው ። የቤተ ክህነት ቤተ መጻሕፍት ሠራተኛ በውስጥ ድክመት ይሁን በእርጅና አይታወቅም ። ሰዓት አሳልፈው ይመጣሉ ። እንዲያውም አንዳንድ ቀን ከመጡ በኋላ የቤተ መጻሕፍቱን በር ቆልፈው ቢሮ ለቢሮ ሲሄዱ ጊዜአቸውን ያሳልፋሉ ።

በ2ኛ ደረጃ በየትም ቦታ ያለው ቤተ መጻሕፍት ፀጥታው ሲከበር በቤተ ክህነታችን ግን ሥራ የፈታው ደጀ ጠኚ ሁሉ ተሰብስቦ ልክ ከጠጅ ቤት ባልተሻለ ሁኔታ ሐሜታውና ውካታው አንባቢውን ሲያባርር ይኖራል ። ያም ሆነ ይህ ላለፈው ክረምት ቤት አይሠራ ምና አሁን የማሳስበው

1. በቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ ያሉት ትርፍ የሽያጭ መጻሕፍት ወጥተው ወደ ሌላ ቤ/መጻሕፍት እንዲዛወሩ ።

2. የቤተ መጻሕፍቱ ጽዳትና መቀመጫዎች በደንብ እንዲዘጋጁ

3. ቢቻል ሠራተኞች አንድ ከመሆን 2 ቢሆኑ

4. በቤተ መጻሕፍቱ ፍጹም ፀጥታ እንዲኖር ነው ። ከዚህም ጋር በጋዜጦችና በመጽሔቶች በጠቅላይ ቤተ ክህነታችን ቤተ መጻሕፍት መኖሩን መግለጥና ማሳወቅ የቤተ ክርስቲያናችን ሥራ መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል ።

ከታዛቢዎች አንዱ ተስፋዬ የሺጥላ
አዲስ አበባ

አቶ ተስፋዬ የሺጥላ ጥያቄዎ እጅግ መልካም ነው ። እንደርስዎ ስለዚሁ ቤተ መጻሕፍት ብዙ ተመሳሳይ ጥያቄ ደርሶናል ነገር ግን ወደ ችግሩ ከመግባታችን በፊት የቤተ መጻሕፍቱ ኃላፊ መልስ እንዲሰጡበት የርስዎን ጥያቄ በሙሉ አውጥተነዋል ።

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

አስቀድሜ በጌታችን በኢየሱስ ስም ሰላምታ አቀርባለሁ ።

“ሰው ዳግም ካልተወለደ በስተቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም” (ዮሐ.3-3) የሚለው ጥቅስ ስላልገባኝ እንድታስረዱኝ በትሕትና እጠይቃለሁ ።

እሸቱ ሀብተ ወልድ
ከከፍተኛ 10 ቀበሌ 05
አዲስ አበባ

● እሸቱ ሀብተ ወልድ ጥሩ ጥያቄ አቅርበሃል ። ይህንን ጥያቄህን ከሁለት ሺህ ዓመታት ገደማ በፊት ኒቆዲሞስ የተባለው የእስራኤል ምሁር ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አቅርቦት ነበር ።

ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም ለሚለው ቃለ መጠይቅ ክርስቶስ የሰጠው መልስ ሰው ካደገና ከጐለመሰ በኋላ እንደገና ወደ እናቱ ማሕፀን ገብቶ ወደ አባቱ አብራክ ተመልሶ ይወለዳል ፤ ማለት ሳይሆን ዳግመኛ ካልተወለደ ማለት ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ማለት ነው ብሎ አስረድቶታል ።

ይሁን እንጂ ይህንን ቃል ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ ቢነግረውም ምሥጢሩ ስላልገባው ተከራክሮበት ነበር ክርስቶስ በመጨረሻ የሰጠው ማስረጃ ነፋስ ወደ ወደደው ይነፍሳል ነገር ግን ከዚህ ቦታ ተነሥቶ ወደ ዚህ ቦታ ይገባል ብሎ ቦታውን ለማወቅ አይቻልም ሁለተኛ ከመንፈስ ቅዱስ የሚወለዱትም ልደት እንደዚህ ነው በማለት አብራርቶ አስረድቶታል ።

እሸቱ ሀብተወልድ ላቀረብከው ጥያቄ እኛ የምንሰጠው መልስም ከዚህ የተለየ አይደለም እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥነ ሥርዓት የሰው ልጆች በተወለዱ ወንዱ በ40 ቀን ሴቷ በ80 ቀን በተጠመቁ ጊዜ ከሥላሴ ልጅነትን ያገኛሉ ከሥላሴ ባገኙትም ልጅነት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ይችላሉ ።

ስለዚህ ሁለተኛ መወለድ ማለት በጥ

ወደ ገጽ ፲፭ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# አንዲት ጥምቀት

ኃጢአትን ለማስተሥረይ ልጅነትን ለማሰጠት የምትሆን ጥምቀት አንዲት ናት ። አንድ ጊዜ ብቻ ትፈጸማለች ። በኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ዘንድ እንደ አይሁድ አይነቱ የበዛ ሥርዐተ ጥምቀት የለም ። ጥምቀት ፡- በዐርባ ቀን በሰማንያም ቀን በአርባ ዓመት ወይም በሰማንያ አመት ብትፈጸም አንዲት ናት ። ጥምቀት ፡- በቄስ በመነኮስ በጳጳስ ወይም በሊቀ ጳጳስ ብትከናወን አንዲት ናት ። ጥምቀት በእፍኝ ውሃ በወራጅ ውሃ ወይም በባሕር ውሃ ብትሆን አንዲት ናት ። አንድ ጊዜ የተጠመቀ በኃጢአት ቢሰናከል ዳግመኛ ጥምቀት አያስፈልገውም ግን ንስሐ መግባት ይገባዋል ። “ የጥምቀት ውሃ አንድ ጊዜ የልቅሶ (የንስሐ) ውሃ ግን ብዙ ጊዜ አድርግ” ተብሎአልና ። (ስማ እስራኤል ገጽ 44ቁ. 52)

በሕጻንነታቸው የተጠመቁ ካደጉ በኋላ መጠመቅ አያስፈልጋቸውም ። ግን በሕጻንነታቸው እንደ ተጠመቁ በጥምቀትም የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆኑ ሊያምኑና ሊረዱ ይገባቸዋል ። በጥምቀት ዳግመኛ መወለድ ከሥጋዊ ልደት ጋር ይነጻጸራል ። አንድ ሕጻን ከእናቱ ማሕጸን በሚወለድ ጊዜ አያውቅም ስለዚህም ካደገ በኋላ ወደ እናቱ ማኅጸን ተመልሶ እንደገና በመውጣት ልደቱን ማረጋገጥ አይችልም ። እንደዚሁም በሕጻንነታቸውና ብዙ ትምህርተ ክርስትና ሳይማሩ የተጠመቁ ካደጉና ከተማሩ በኋላ እንደገና በመጠመቅ ከእግዚአብሔር ልጅነትን ሊያገኙ አይችሉም ። ግን የሕጻንነት ጥምቀታቸውን በወላጆችና በክርስትና አባትና እናት አማካኝነት ማመን ይገባቸዋል ።

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት በየዓመቱ የጥምቀት በዓል በወንዝ ዳር ይከበራል ምእመናንም በባሕረ ጥምቀቱ ውሃ ይረጫሉ ይህን በማየት አንዳንድ የውጭ አገር ሰዎች እኛ ኢትዮጵያውያን ጥምቀታችንን በየዓመቱ እንደምናድስ ወይም እንደምንከልስ አስመስለው መገመታቸው አልቀረም።ግን ልክ አይደሉም ። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ የጥምቀትን በዓል በደመቀ ሁኔታ ማክበርዋ መድኃኒታችን ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት በዮሐንስ እጅ መጠመቁን በሥዕል ወይም በሚታይና በሚስተዋል መንገድ ለማሳየት እንጂ የምእምናኖችዋን ጥምቀት ለማደስ እንዳልሆነ ማስተዋል ያስፈልጋል ። ለምሳሌ ምሥራቃውያንም ሆኑ ምዕራባውያን የልደትን (የገናን) በዓል ሲያከብሩ በቤተክርስቲያንም ሆነ በቤታቸው ውስጥ ግርግም ይሠራሉ ። ድንጋይ ይኮለኩላሉ የዛፍ ግንጣፊ ያቆማሉ በውስጡም ድንግል ማርያም ሕጻኑ ክርስቶስን እንደያዘች የሚያሳይ ቅርጽ ያኖራሉ ። በአጠገቡም እንስሳት እንዳሉ የሚያሳይ ቅርጽ ያስቀምጣሉ እንግዲህ ይህ ሁሉ ድርጊት ክርስቶስ በበረት ውስጥ እንደተወለደ በምሳሌ ለማሳየት እንጂ በእየዓመቱ ክርስቶስ በበረት እንደሚወለድ ያምናሉ ማለት አይደለም ።

ከዚህም ሌላ ክርስቲያኖች ሁሉ በየዓመቱ የስቅለትን በዓል ሲያከብሩ በዕለተ ዐርብ እንደተሰቀለ የሚያሳይ ሆኖ ክርስቶስን የሚያሳይ ስዕለ ስቅለት ያቆማሉ ። በዚህም ጊዜ ክርስቶስ በየዓመቱ እንደሚሰቀል የሚያምኑ ክርስቲያኖች እንደአሉ አድርጎ የሚያወራ ቢኖር እርሱ የዋህ ነው ።

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ የጥምቀት አከባበር ልክ ከላይ እንደገለጥናቸው ምሳሌዎች ነው ። ካህናትና ምእመናን ንዋያተ ቅድሳትን ይዘው ከ ቤተ ክርስቲያን ወደ ባሕረ ጥምቀት መውረዳቸው ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መሄዱን ያመለክታል ። ምእመናን ሁሉ በባሕረ ጥምቀቱ ውሃ መረጩታቸው ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ውሃ መጠመቁንና የእኛ ጥምቀት በክርስቶስ ጥምቀት መቀደሱን ያሳያል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመድኃኒታችን የክርስቶስ ጥምቀት ለክርስቲያኖች ጥምቀት መሠረት በመሆኑ በጉሉህ ድርጊት ታከብረዋለች ። እርግጥ አንዳንድ ክርስቲያኖች የሥጋዊ ልደት በዓላቸውን እንደሚያከብሩ በጥምቀት ከእግዚአብሔር የተወለዱበትንም ዕለት በየዓመቱ ያከብራሉ ። ሆኖም ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ እግዚአብሔርን በማመስገን ነው እንጂ በየዓመቱ በመጠመቅ ወይም በመረጨት አይደለም ። ሥጋዊ ልደት አንድ ጊዜ እንደሆነ መንፈሳዊ ልደትን የምታሰጥ ጥምቀትም አንድ ጊዜ ብቻ ናትና ።



# ትምህርተ ሥላሴ



ዓለማተ ዓለም ሥላሴ ዘአልብከሙ ዓለም ።

ለክርስትና እምነት መሠረቱ ማእከሉና መደምደሚያው ምሥጢረ ሥላሴ ነው ። ክርስትና የተመሠረተ በእግዚአብሔር ሦስትነት መገለጥ ላይ ነውና ። እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ከመሆኑ በፊት ትምህርተ ሥላሴን ያወቀና የተረዳ ማንም አልነበረም ። እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ከተወለደ ወዲህ ግን በእግዚአብሔር አንድነት ሦስትነት ፡ በሦስትነትም አንድነት መኖሩ ተገለጠ ።

ስለ እግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት የሚሰጠውን ትምህርት ምንም እንኳ የፍጡር አእምሮ መርምሮ ሊረዳው የማይችል ቢሆንም ከእግዚአብሔር የተገለጠ እውነት ነው ። ይህም እውነት በክርስቲያኖች ዘንድ ጸንቶ ይኖራል ። ምክንያቱም ከክርስትና ሃይማኖት ልዩነት ያላቸው ሃይማኖቶች ሁሉ እግዚአብሔር አንድ ገጽ አንድ አካል ብቻ እንደሆነ ሲያስተምሩ የክርስትና ሃይማኖት ግን እግዚአብሔር በአንድነትና በሦስትነት የነበረ ያለና የሚኖር መሆኑን ያስተምራል ።

የአሕዛብ ሃይማኖት ብዙኀን አማልክት እንዳሉ ሲያስተምር የክርስትና ሃይማኖት ግን እግዚአብሔር በሦስትነት ቢገለጥም አንድ አምላክ ነው እንጂ ሦስት አማልክት አለመሆኑን ያረጋግጣል ። ከዚህም ጋር ሌሎች ሃይማኖታውያን እግዚአብሔር አካላዊ ያልሆነ ዝርው ኃይል ስሜታዊ ነገር እንደሆነ ሲያምኑና ሲያስተምሩ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ግን እግዚአብሔር ረቂቅ (መንፈስ) ቢሆንም በፈቀደ ጊዜ በፈቀደው መንገድ ለወደደው ፍጥረት መገለጥ የሚችል አካላዊ መንፈስ መሆኑን ያስተምራል ።

እግዚአብሔር በባሕርይ በመለኮት በሥልጣን በመፍጠር ወዘተ ... አንድ ነው ። ይህም በቅዱሳት መጻሕፍት የተመሰከረ ጽድቀ ሃይማኖት ነው ። ስለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች እናስተውል “እስራኤል ሆይ ስማ ፥ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው” (ዘዳግም 6 ፡ 4) “ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው” (1ቆሮ. 12 ፡ 6) ። “አንድ እግዚአብሔር አለ...” (1ጢሞ 2 ፡ 5) ። በዚህና ይህን በመሳሰሉ ማስረጃ ጥቅሶች ሁሉ ስለ እግዚአብሔር አንድነት ለመረዳት እንችላለን ።

እግዚአብሔር በስም በአካል በግብር ሦስትነት አለው ። የስም ሦስትነት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ነው ። አብ ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ ተብሎ አይጠራም ። ወልድም አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ ተብሎ አይጠራም ። መንፈስ ቅዱስም አብ ወይም ወልድ ተብሎ አይጠራም ። እርግጥ እግዚአብሔር በሚለው ስም ሦስቱም ይጠሩበታል ። (ዮሐ 1፥1-3።የሐዋ. 20፥28።28፥25-27።

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በየራሳቸው ፍጹም አካል አላቸው ግብራቸውም በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረትነት ቅዱሳን ሊቃውንት አብራርተው እንደ አስረዱ የአብ ግብሩ ወላዲነትና አሥራፂነት ነው የወልድ ግብሩ ተወላዲነት ነው ። የመንፈስ ቅዱስም ግብሩ ሠራፂነት ነው ።

ትምህርተ ሥላሴ የሰዎች ፍልስፍና ሳይሆን ብሉይና ሐዲስ ኪዳናት በግልጥ የሚያስተምሩት እውነተኛ ትምህርት አምላካዊ ክሥተት ነው ።

ለምሳሌ ራሱ እግዚአብሔር ሲናገር እንዲህ ይላል “ሰውን በምሳሌያችን እንፍጠር ”(ዘፍጥ.1፥26) “ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለምና ረዳት እንፍጠርለት” (ዘፍጥ. 2፥18) “አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ” (ዘፍጥ 3፥22) “ኑ እንውረድ” (ዘፍጥ. 11፥7)



www.ethiopianorthodox.org

"እግዚአብሔርም አለ ማን ይሄድል ናል" (ኢሳ. 6፡8)።

እነዚህ ጥቅሶች የእግዚአብሔርን የአካል ሦስትነት ያመለክታሉ። ሆኖም ከአንድ በላይ የሆነ ቁጥርን ያመለክታሉ እንጂ በሦስት የተወሰነ ቁጥርን ኢያሳዩም የሚል ሀሳብ ይኖር ይሆናል። እዎ እዚህ ላይ ግልጥ ባይመስልም በሌላ አንቀጽ በሁለት ያልሆነ ከሦስት ያልወጣ ግን በሶስት ብቻ የተወሰነ ጥቅስ እናገኛለን።

እግዚአብሔር አምላክ ለሙሴ በተገለጠ ጊዜ እንዲህ አለ" እኔ እግዚአብሔር የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ" (ዘጸአ. 3፡6) በትንቢተ ኢሳይያስ እንደተገለጠው መላእክት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአ ፀባዖት..." በማለት ሲያመሰግኑ ተሰምተዋል። (ኢሳ. 6.3)።

በብሉይ ኪዳን ስለ እግዚአብሔር ሦስትነት የተነበበው ሁሉ በሐዲስ ኪዳን ትክክልና ግልጥ የሆነ ትርጉም አግኝቶአል። ለምሳሌ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆኖ በ30 ዓመቱ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ እግዚአብሔር አብ በደመና ውስጥ "የምወደው ልጄ ይህ ነው" ሲል ተሰማ። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ በራሱ ላይ ዐርፎ ታየ (ማቴ. 3.15-17)።

ይህም የአካል ሦስትነትን ይገልጥልናል። በመጨረሻም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ "በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ" (ማቴ. 28፡19-20) ሲል ትእዛዝ ሰጠ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ትምህርተ ሥላሴን ሲያስረዳ "የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔር አብ ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም አንድነት ከሁላችሁ ጋር ይሁን"(2ቆሮ. 13፡14) ብሎአል። ይህም ሁሉ የስምና የአካል ሦስትነትን በጉልህ ያስተምራል። ትምህርተ ሥላሴን የሚያስረዱ ሌሎችም የሐዲስ ኪዳን ጥቅሶች ይገኛሉ። ለምሳሌ 1 ቆሮ. 12፡4-6። ኤፌ. 2፡20 - 22። 1ጴጥ.1፡1 -2 ወዘተ...።

ሊቃውንትም የብሉይና የሐዲስ ኪዳናትን ትምህርት መሠረት በማድረግ "እንዘ አሐዱ ሠለስቱ ወእንዘ ሠለስቱ አሐዱ ይሤለሱ በአካላት ወይትዋሐዱ በመለኮት። አንድ ሲሆኑ ሦስት ናቸው ሦስትም ሲሆኑ አንድ ናቸው። በአካላት ሦስት ይሆናሉ። በመለኮት ግን አንድ ይሆናሉ"።

"ምሥጢረ ሥላሴ ይትከፈል ወኢይትከፈል የሦስትነት ምሥጢር ይከፈላል አይከፈልምም" በማለት ስለ ሥላሴ ሰፋ ያለና ጥልቅ ምሥጢር ያለው ትምህርት አስተምረዋል ጽፈዋልም።

በአራተኛው ምእት ዓመት የነበረው የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አትናቴዎስም ስለ ትምህርተ ሥላሴ "የአትናቴዎስ" እየተባለ በሚጠራው ሥርዐተ ሃይማኖት (ክሪድ) እንደሚከተለው አስተምሮአል።

"ለመዳን ፈቃደኛነት ያለው ሰው ሁሉ በሁሉ ዘንድ ያለቸው ቤተ ክርስቲያን የምታምነውን ይህን ሃይማኖት ይጠብቅ ዘንድ ይገባዋል። ደኅንነትን እንዳያጣ ይህን እምነት መያዝ ያስፈልገዋልና።

በሁሉ ዘንድ ያለቸው ቤተ ክርስቲያን የምታምነውም ሃይማኖት ይህ ነው አካላትን ሳንደባልቅ ባሕርይንም ሳንከፍል አንዱን አምላክ በሦስትነት ሦስትነትንም በአንድነት እናመልክ ዘንድ ነው።

አንዱ አካል የአብ ነው። ሁለተኛውም የወልድ ነው። ሦስተኛውም የመንፈስ ቅዱስ ነው።

ነገር ግን የአብና የወልድ የመንፈስ ቅዱስም አምላክነት አንዲት ናት። ክብራቸው እኩል ነው ግርማቸውም ዘለዓለማዊ ነው።

አብ እንዳለ እንዲሁም ወልድ አለ መንፈስ ቅዱስም አለ።

አብ አልተፈጠረም ወልድም አልተፈጠረም መንፈስ ቅዱስም አልተፈጠረም።

አብ አይወሰንም ወልድም አይወሰንም መንፈስ ቅዱስም አይወሰንም።

አብ ዘለዓለማዊ ነው፣ ወልድ ዘለዓለማዊ ነው፣ መንፈስ ቅዱስም ዘለዓለማዊ ነው።

ግን በዘለዓለማዊነት ያለ አንድ ነው እንጂ ሦስት ዘለዓለማውያን (አማልክት) ናቸው አንልም። እንደዚሁም የማይወሰንና ያልተፈጠረ አንድ ነው እንጂ የማይወሰኑና ያልተፈጠሩ ሦስት ናቸው አንልም።

እንደዚሁም አብ ሁሉን ቻይ ነው ወልድም ሁሉን ቻይ ነው መንፈስ ቅዱስም ሁሉን ቻይ ነው።

ነገር ግን ሁሉን የሚችል አንድ ነው እንላለን እንጂ ሦስት ሁሉን ቻዮች አንልም። እንደዚሁም አብ አምላክ ነው ወልድም አምላክ ነው። መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው። ነገር ግን አንድ አምላክ ነው እንጂ ሦስት አማልክት አንልም። እንደዚሁም አብ ጌታ ነው፤ ወልድም ጌታ ነው መንፈስ ቅዱስም ጌታ ነው። ስለሆነም አንድ ጌታ እንጂ ሦስት ጌቶች አንልም።

በክርስትና እውነትነት እንደምንለው አካል ሁሉ እያንዳንዱ በየራሱ አምላክና ጌታ ሆኖ ሳለ ሦስት አማልክትና ሦስት ጌቶች ከማለት የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን እምልኮ እምነት ትከለክለናለች።

አብ ከማንም አልተሠራም አልተፈጠረም አልተወለደም ወልድም በአብ ነው ስለሆነም ተወልዶ ነው እንጂ ተሠርቶ ወይም ተፈጥሮ አይደለም መንፈስ ቅዱስም በአብ ነው ዳሩ ግን ሠርፆ እንጂ ተሠርቶ ወይም ተፈጥሮ ወይም ተወልዶ አይደለም።

እንግዲህ አንድ አብ አለ እንጂ ሦስት አባቶች የሉም። አንድ ወልድ አለ እንጂ ሦስት ወልዶች የሉም። አንድ መንፈስ ቅዱስ አለ እንጂ ሦስት መንፈስ ቅዱሶች የሉም።

በዚችም ሦስትነት መቅደምም መከታተልም የለም። ከቢፁ (ከኳደኛው) የሚበልጥና የሚያንስ የለም። ሦስቱ አካላት እየራሳቸው የአንዲት ዘለዓለማዊነት ናቸው። እየራሳቸውም እኩል ናቸው እንግዲያውስ እንደተባለው ሁሉ ሥላሴን በአንድነት፣ አንድነትንም በሥላሴ ማመን ይገባል።

መዳንን የሚፈልግ ስለ ሥላሴ እንደዚሁ ያስብ ...."

ይህ የቅዱስ አትናቴዎስ ሥርዐተ ሃይማኖት ከሐዋርያትና ከ318 ሊቃውንት ሥርዐተ ሃይማኖት ጋር ተቀባይነት ያለው በመሆኑ በዓለም ያለችው ቤተ ክርስቲያን ስለ ትምህርተ ሥላሴ በማስረጃነት ትጠቅሰዋለች። በጸሎተ ቅዳሴም ጊዜ ስለ ሥላሴ ያላትን እምነት ትመሰክርበታለች። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ይህን የአትናቴዎስን ሥርዐተ ሃይማኖት ስለ ምሥጢረ ሥላሴ ለማስረጃነት ትቀበለዋለች። ግን በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ እስካሁን ድረስ አልተጠቀመችበትም።

ይህን ጽሑፍ ከማጠቃለላችን በፊት ሊቃውንት ስለ ትምህርተ ሥላሴ ካቀረቡአቸው ምሳሌዎች አንዳንዶችን እንመለከታለን።


1ኛ ፀሐይ፡ ለፀሐይ ሦስት ሁኔታዎች አሉት ሀ ክበብ ለ ብርሃን፣ ሐ ሙቀት ናቸው።

2ኛ እሳት፣ ለእሳት ሦስት ሁኔታዎች አሉት። ሀ ነበልባል፣ ለ ብርሃን ሐ ዋእይ (ሙቀት) ናቸው። እነዚህ ሦስት ሁኔታዎች ከፀሐይ ወይም ከእሳት ሲገኙ ተከፍሎ ወይም ተድኅሮ የለባቸውም ፀሐይ ወይም እሳት ደግሞ ያለ ሦስቱ ሁኔታዎች አይኖርም። በሌላም በኩል ፀሐይ በክበቡ በብርሃኑና በሙቀቱ ምክንያት ሦስት ፀሐዮች አይባልም። ግን አንድ ፀሐይ ነው። እሳትም በሦስቱ ሁኔታዎች በነበልባሉ በብርሃኑና በሙቀቱ ምክንያት ሦስት እሳቶች አይባልም። ግን አንድ እሳት ይባላል (ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት ቁ. 47 - 48)።

አብ በነበልባሉ ወልድ በብርሃኑ መንፈስ ቅዱስም በዋእዩ (በሙቀቱ) ይመሰላል። እነዚህም ከላይ በጠቀስነው ምሳሌ ረገድ አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይባሉም።

ስለ ትምህርተ ሥላሴ በዚህ አነስተኛ ጽሑፍ መፈጸም አንችልም። ለመጻፍ ብንደፍርም አእምሮአችን ውሱን ስለ ሆነ መጠንቀቅ ያስቸግረናል። ነገር ግን




መጻሕፍት የሚነግሩንን ሊቃውንት ያስተማሩንን እኛም የምናምነውን በአጭሩ አቅርበናል።

ትምህርተ ሥላሴን ለመቃወም ሲሉ እግዚአብሔር እንደ ገባሬ ትርኢት በአንድ ጊዜ አብ በሌላ ጊዜ ወልድ እንደገናም በሦስተኛ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እየሆነ ይገለጣል እንጂ አንድ ገጽ ነው። በአካላትም ሦስትነት የለውም የሚሉ ሰባልዮሳውያን በቤተ ክርስቲያናችን ተቀባይነት የላቸውም። እንደዚሁም በሦስቱ አካላት ዘንድ መዐርግ እንዳለ ማለት መበላለጥ መቀዳደምና መከታተል ያለ አስመስለው የሚያስተምሩ የአርጌኒሳውያንንም ትምህርት አንቀበልም። እግዚአብሔርን አንድ ገጽ አድርገው ወልድን እንደፍጡር መንፈስ ቅዱስንም እንደ ኃይል በመቁጠር የሚያስተምሩትንም ክፍሎች እንቃወማለን ምክንያቱም ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ሦስቱ አካላት ቀዋምያንነትና ዘለዓለማውያንነት በግልጥ ያስተምራሉና። (ዮሐ. 10፡30። 14፡6-11፤ 15፡26። የሐዋ.2፡38-39።5፡30-32።7፡55 - 56። 1 ዮሐ. 2፡23)።

ትምህርተ ሥላሴ በእግዚአብሔር የተገለጠ በመጻሕፍት የተመሰከረ በሊቃውንት የተብራራ እውነት ስለሆነ ይህንን እውነት እናምናለን፤ እናሳምናለን እንማራለን እናስተምራለን። እግዚአብሔር ከዓለም በፊት እስከዘለዓለም ድረስ በአንድነትና በሦስትነት ሲቀደስና ሲመሰገን የነበረ ያለና የሚኖር አምላክ እንደሆነ እንመሰክራለን።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

——— ፲፩ ———





www.ethiopianorthodox.org

# ታቦትና ክብሩ



በአለቃ አያሌው ታምሩ

ታቦት በእግዚአብሔር ፈቃድ የአምልኮት ምስክር ሆኖ የሚኖር በቤተ መቅደስ ካሉት ንዋያተ ቅድሳት የተለየ ክብርና ታሪክ ያለው የአምልኮተ እግዚአብሔር መግለጫ ነው ። ስለ ሁኔታው በምንወያይበት ጊዜ ታቦት ከየት መጣ? የአምልኮት ምስክርነቱስ መቸ ተጀመረ ? ብሎ መጠየቅ እውነትነት አለው ።

ስለዚህ የሚከተለውን እናያለን ። የሰው ልጅ አምላክ ለመሆን ሽቶ የማይገባውን ሠርቶ ሳይሆንለት ሲቀር ገጸ እግዚአብሔርን እንኳን ማየት ስለተከለከለ በተሰደደበት የፍዳ መቀበያ ምድር ሁሉ ነገር እየከበደው ፍርሃት ድንጋጼ ሐዘን ትካዜ እየተጫነው በመሄዱ አምላክን መፈለግ ጀመረ ። ግን አእምሮው በኃጢአት ስለደፈረሰና አሳሳቹ ዲያብሎስ ከአጠገቡ ስለአልራቀ እውነተኛውን ነገር አተኩሮ መመልከት መመርመርና ማወቅ ተሳነው ። በዚህ ምክንያት የልብ አምሮቱ ባረፈበት መጠን የሰማይ ሠራዊትን ፀሐይ ጨረቃን ከዋክብትን በባሕር በየብስ ያሉትን ዓሣ አንበሪን አዞውን ጉማሬውን እንስሳውን አውሬውን ወፉን እያስመሰለ እንጨት እየጠረበ ድንጊያ እያለዘበ ምሳሌ መመሰል ጣዖት ማቆም ያንን ማምለክ ለዚህ መስገድ መበርከክ ጀመረ ።

እግዚአብሔርን አላውቅም እንደ ማለቱና እምቢተኛ እንደመሆኑ መጠን ይህን የማይገባውን እንዲህ በመሥራት በሚርት በጣዖት አምላኩን በደለ ራሱን አታለለ እግዚአብሔር ግን ቸል አላለውም ። እንደ መላእክት በአእምሮ ጠባይዕ ክፉን ከበጎ ለይቶ ከክፉ ርቆ መልካሙን ጠብቆ በሕገ ልቡና መኖር ቢሳነው በቀለምና በወረቀት የሚመራበት ሕገ መጽሐፍን እንዲሰጠው አሁንም ረቂቁን አምላክ ማወቅ ተስኖት በማዙፍ ነገር ሲደናገር ቢያየው ኋላ ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ እስኪገለጥለት ድረስ ለአምልኮቱ ምስክር የሚሆን ጽላትን ታቦትን ሰጠው ።

መሠረቱ እንዲህ ነበረ ። ዘመኑ ከክርስቶስ ልደት በፊት አንድ ሺ ሰባት መቶ ዓመታት ገደማ ይሆናል ። ጊዜው ልዑል እግዚአብሔር እውነተኛ ወዳጁን አብርሃምን አስቦ ልጆቹን በረድኤት የጎበኘበት ከመገዛት ነፃ ያወጣበት ሲሆን ከዚያውም ነፃነታቸውን ካገኙ ሁለተኛ ዓመታቸው ነበር ። ሕዝቡ በታላቁ አምላካችን ረድኤት ጥበቃ ስር ሳሉ አምልኮቱን ረሱ ኪዳኑን ጣሱ የወርቅ ጥጃ ሠርተው ጣዖት አቆሙ አምላካችን ብለው ሰየሙ ከዚያ በኋላ ይህ ነገር እየቀጠለ እንዳይሄድ የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን ብቻ እንዲያመልክ ይህም ከትውልድ ወደ ትውልድ ሕግ ሆኖ እንዲኖር በሙሴ አማካኝነት ትእዛዙ የተጻፈበትን ጽላት ሰጣቸው ።

ለጽላቱም ታቦት እንዲዘጋጅ አደረገ ። ጽላት ሕጉ የተጻፈበት ሰሌዳ ሲሆን ታቦት ደግሞ ጽላቱ የሚኖርበት ንዋየ ቅድሳት ነው ። በብሉይ ኪዳን የነበረው የሥራ አቋም ይህ ነው ።

ስለ ጽላት ብሉይ ኪዳንን ስንመረምር ሙሴ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር እጅ የተቀረጹና ትእዛዙ የተጻፈባቸው ሁለት ጽላቶች ከልዑል እግዚአብሔር እንደተቀበለ ኋላ ደግሞ እነዚህ ቢሰበሩ እንደገና ቅረጽ ሲል በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ሙሴ ጽላቶቹን እንደቀረጸና በጽላቶች ላይ የነበረውን ጽሑፍ ግን እሱ ራሱ እግዚአብሔር እንደገና እንደ ጻፈለት እንረዳለን ሙሴ ጽላቶቹን ለመቀበል ባደረገው ደጅ ጥናት 40 መዓልት 40 ሌሊት እንደ ጾመ ተገል ጿል ።

ስለ ታቦት ደግሞ ከማይነቅዝ እንጨት ታቦትን ሥራ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ከሥንዝር ቁመቱ ክንድ ከስንዝር ወርዱ ክንድ ከሥንዝር ይሁን መግጠሚያ አብጅለት በመግጠሚያው ላይ ሁለቱን ኪሩቤል ፊት ለፊት እንዲተያዩ አድርገህ ከንጹሕ ቅጥቅጥ ወርቅ ሠርተህ በመግጠሚያው በግራና በቀኝ አድርጋቸው ። ክንፋቸውን ዘርግተው ረበው መግጠሚያውን የሚሸፍኑ ይሁኑ በመካከል ባለው ክፍት ቦታ እኔ ከዚያ ተገልጬ አነጋግርሀለሁ ሲል ልዑል እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ የተመላበትን ትእዛዝ እናነባለን ።

ሙሴም እንደታዘዘ አድርጓል ከዚህ በኋላ ጽላትን ለብቻ ታቦትን ለብቻ ለይቶ የሚጠራ አናገኝም ። በጠቅላላ አጠራሩ ስሙ ታቦተ እግዚአብሔር ታቦተ ሕግ ታቦተ ኪዳን ታቦተ ስምዕ የሚልና ይህን የመሳሰለው ነው ። ትርጓሜውም እግዚአብሔር ያደረበት አድሮበት የሚኖር ሕጉ የሚጠበቅበት ኪዳኑ የሚጸናበት አምልኮቱ የሚመሰከርበት ማለት ነው ። ሕዝበ እሥራኤል በዚህ ታቦት አማካኝነት ሁሉን ቻይ የሆነውን ኃያል አምላክ እግዚአብሔርን ሲያመልኩ ሥርዓተ አምልኮት ሲፈጽሙ ኖረዋል ። ካህናት ሌዋውያንም በሕጉ የታዘዘውን መሥዋዕት በዚህ ታቦት ፊት ሲያቀርቡ ጸሎት ሲጸልዩ ትምህርት ሲያስተምሩ የኃጢአትን ሥርየት ሲቀበሉ ሲያሰጡ ኖረዋል ። ልዑል እግዚአብሔርም የሰጠውን ቃል ሳይለውጥ መሥዋዕታቸውን ጸሎታቸውን እየተቀበለ ቃል በቃል ሲያነጋግራቸው ታላላቅ ተአምራት ሲያደርግላቸው ኖሮአል ። ከተአምራቱ አንዱም ለዛሬው በዓል በምሳሌነት ቀድሞ የተገኘው በኢያሱ ዘመን በዮርዳኖስ ወንዝ የተፈጸመ ነው ። እሥራኤል ጉዞአቸውን ከግብጽ ወደ ከነዓን እንደቀጠሉ በመንገድ ላይ ናቸው ። ሆኖም ከተሰጣቸው ተስፋ ፈለግማውን የዳረጎት ያህል ከዮርዳኖስ ወዲህ ማዶ የሚገኘውን የአግን የሲኦንን አገር እጅ አርገው ተረክበዋል ።

ሙሴ ሞቶአል ። ኢያሱ በስፍራው ተተክቶ መሪነቱን ይዞአል ። ሕዝቡ ሙሴን በማጣታቸው ያዘኑ ከመሆናቸውም በላይ ልዑል እግዚአብሔር በሙሴ አድሮ ሲረዳቸው እንደኖረ ከዚያም በኋላ በተከታዮቹ አድሮ ይረዳቸው እንደሆን የሃይማኖት ምልክት ለማግኘት የሚያሰላስሉበት ጊዜ ነበረ ። በዚህ ጊዜ ሰው ቢሞት አብሮ የማይሞተው ምን ጊዜም የማይለወጠው ሁሉን አሳልፎ የሚኖረው ሥራ የማያልቅበት ክብሩ የማይደፈረው ሥልጣኑ የማይገሠሰው ቃሉ የማይታጠፈው ኃያል አምላክ እግዚአብሔር አይዞህ በርታ ጽና ከሙሴ ጋር እንደነበርኩ ከአንተም ጋር አለሁ ። ይህን ሕዝብ ዮርዳኖስን ታሻግረዋለህ ። ለአባቶቻችሁ ወደ ማልኩለት አገር ታገባዋለህ ከዛሬ ጀምሮ በሕዝቡ ፊት ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ ። እስከ ሦስት ቀን ዮርዳኖስን ይሻገራሉና ሕዝቡን አዘጋጃቸው ሲል ኢያሱን አነጋገረው አዘዘው ። ኢያሱም ትእዛዙን ከተቀበለ በኋላ ሕዝቡ እስከ ሦስት ቀን ዮርዳኖስን የሚሻገር መሆኑን አውቆ ልብሱን አጥቦ ሰውነቱን አንጽቶ እንዲጠባበቅ አዘዘ ። በሦስተኛውም ቀን ማታውን ወደ ዮርዳኖስ ወርደው ከዮርዳኖስ ወንዝ ዳር ሰፍረው አደሩ ።

ወሩም ጥር ዕለቱ ጥር 10 ለ11 አጥቢያ እንደሆነ ይነገራል ። ዮርዳኖስ ሞልቶ ነበርስትነሥ የእግዚአብሔርን ታቦት ጉዞ ተመልከቱ ። ይህን መንገድ ከዚህ በፊት አታውቁትምና የእግዚአብሔርን ታቦት የተሸከሙ ሲቀድሙላችሁ የሰልፍ ተራችሁን ጠብቃችሁ ተከተሉ ።

ማንም ሰው ወደ እግዚአብሔር ታቦት አይቅረብ በእግዚአብሔር ታቦትና በሕዝቡ መካከል 2ሺ ክንድ ርቀት ይኑር ። የእግዚአብሔርን ታቦት የተሸከማችሁ ካህናትም ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ በገባችሁ ጊዜ ከውሀው ላይ ቁሙ ሲል መምሪያ ትእዛዝ ለኢያሱ ሰጠ ። ሕዝቡም እንደታዘዙ አደረጉ በማግሥቱ ጧት ተነሥተው የእግዚአብሔርን ታቦት የተሸከሙ ካህናት በፊት በፊት መሪያቸው በመሀል ሕዝቡ በኋላ በኋላ እየ ተከተሉ ጉዞ ጀመሩ ። የእግዚአብሔርን ታቦት የተሸከሙ ካህናትም ወደ ዮርዳኖስ ደርሰው ከወንዝ ሲገቡ እግራቸው መጀመሪያ ውሃ ሲረግጥ ዮርዳኖስ ተከፈለ ። ወደታች የሚሄደው ውሃ ወርዶ አለቀ ። ከጨው ባሕር ገባ ቦታውም ባዶ ሆነ ።

ከላይ ያለው ውኃም ከመውረድ ታግዶና ተገቶ ቆመ ። ወደላይ እንደ ክምር እየተቆለለ ከላይ እስከ ቀራትያምር ድረስ ።

ሕዝቡም ከወደላይ እንደግድግዳ የቆመውን እንደ ክምር የተቆለለውን ውኃ እያዩ ከታች ውኃው የለቀቀውን አሸዋ የተከፈተላቸውንም መንገድ እየተመለከቱ የእግዚአብሔር ታቦት ከወንዙ መሀል ቆሞላቸው የእግዚአብሔርን ቸርነት እያደነቁ በሃይማኖት ዮርዳኖስን ተሻገሩ ። የሕዝቡም ቁጥር ከሴት ከልጅ ሌላ ለሰልፍ የደረሰው ከ20 ዘመን በላይ የሆነው ስድስት መቶ አምስት ሺ አምስት መቶ ነበሩ ።

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ኢያሱን የካህናት እግር የቆመበት ከዮሰዳኖስ ባሕር መሀል ዐሥራ ሁለት ድንጊያ አውጥታችሁ ዛሬ በምታድሩበት ቦታ ትከሉት ከውጭም 12 ድንጊያ አውጥታችሁ ዛሬ በምታድሩበት ቦታ ትከሉት ከውጭም 12 ድንጊያ አምጥታችሁ የካህናት እግር ከቆመበት ከወንዙ መሀል አኑሩአቸው ። ዛሬ ላደረግሁላችሁ ሥራ ለልጅ ልጅ መታሰቢያ ይሁን አለው ። ኢያሱም እንደ ታዘዘው አደረገ ።

ይህ በዓል በእግዚአብሔር ቸርነት እስራኤል ዮርዳኖስ ተከፍሎላቸው በደረቅ ተሻግረው ወደ ምድሪ ርስት የገቡበት ቀን ተብሎለእስከ መድኃኒታችን መምጣት ድረስ መታሰቢያው ሲከበር ቆይቶአል ። የመጀመሪያው በዓል አከባበር ምክንያት ይህ ነው ።

ሁለተኛው ደግሞ በመግቢያው እንደገለጽነው ኢያሱ ምሳሌ የሆነለት በታቦት ላይ አድሮ ሕዝቡን መርቶ ዮርዳኖስን አሻግሮ ወደ ርስታቸው ያገባቸው እግዚአብሔር አምላክ ሆኖ ሥጋ ለብሶ ከመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሥርዓተ ሕፃናትን እየፈጸመ አድጎ 30 ዓመት ሲሞላው ጥር 10 ለ11 አጥቢያ ከናዝሬት ከገሊላ ዮሐንስ ወደ አለበት ወደ ዮርዳኖስ መጥቶ አድሮ ከሌሊቱ በ10 ሰዓት በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ አምላክነቱን የገለጸበት ጥምቀትን የቀደሰበት ቀን ነው ።

ከዚህ ጊዜ መድኃኒታችን ከውኃው እንደወጣ ሰማይ ተከፍቶ አብ በደመና ሆኖ ከደመና ላይ የምወደው ልጄ ይህ ነውና እሱን ስሙት ብሎ ሲመሰክር መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ ከራሱ ላይ ሲቀመጥ ምሥጢረ ሥላሴ ስለተገለጸ ሰዎች እግዚአብሔርን በአንድነቱ በሦስትነቱ ለማየት ስለበቁ እግዚአብሔር ሰውን በልጁ እንደታረቀው ታወቀ ተረዳ ተረጋገጠ ። በዚህ በዕለተ ጥምቀት አዳምና ሔዋን ለዲያብሎስ ባርነት ቃል ኪዳን ገብተውበት የነበረው መጽሐፈ ዕዳ ተደመሰሰ ሰው ከርኩስነቱ ተቀደሰ በቀዳማዊ አዳም ተወስዶ የነበረ ልጅነት በዳግማዊ አዳም ተመለሰ ሰው ተገፎ የነበረውን ልብስብርሃን ለበሰ ልጁን የዓለም ቤዛ አድርጎ ለላከ ለአብ በጥምቀቱ ምእመናን ለወልድ ለእውነተኛ ምስክርነት በዮርዳኖስ ለወረደ ለመንፈስ ቅዱስ ምሥጋና ይሁን ሁለተኛው ታሪክ ባጭሩ ይህ ነው ።

እንግዲህ የበዓሉ አከባበር ምክንያት ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሲሆን ታቦት ወደ ወንዝ እያወረዱ በባሕር

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት የሚፋጠኑ እነማን ናቸው ?

አንዳንድ ሰዎች ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት የሚፋጠኑ ባሕታውያን ወይም መነኮሳት ናቸው ይላሉ ለአስተሳሰባቸውም ድጋፍና መረጃ አድርገው የሚያቀርቡት በትዳር ያልተወሰኑ ሰዎች ሚስት አላገቡም ልጅ አልወለዱም ቤት አልሠሩም ንብረት አላበጁምና ለስብከተ ወንጌል በተጠሩ ጊዜ ማቄን ጨርቄን ቤቴን ንብረቴን ሚስቴን ልጆቼን የማለት ጠባይ አይታይባቸውም የሚለውን ነው።

ሌሎች ክፍሎች ደግሞ ትዳር ከሌላቸው መነኮሳት ይልቅ በትዳር የተወሰኑ ቀሳውስትና ዲያቆናት በሕዝብ ዘንድ ታማኝነት አላቸው ኑሯቸውም ከሕዝቡ የተለየ አይደለም በቅርብ ሆነው የሕዝቡን ፍላጎትና ችግር ስለሚያውቁ ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ የሚለውን አሳባቸውን ይሰነዝራሉ።

ያም ሆነ ይህ የወንጌልን ቃል ለማስፋፋት እንቅፋት የሚሆነው ከአሠራሩ ላይ የሚደርሰው ጉድለት ነው እንጂ እገሌ ሚስት አለችውና ለስብከተ ወንጌል አይፋጠንም እገሌ ግን ሚስት ስለሌለችው ቤት ንብረት ስላልመሠረተ ለስብከተ ወንጌል ይፋጠናል በማለት አንዱን ከአንድ አብልጦ ለመናገር ያስቸግራል።

የሰው ልጅ ችሎታው የሚመዘነው በአሠራሩ ነው እንጂ መነኩሴ ወይም ቄስ በመሆኑ አይመስለንም ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ሕጋውያን ቀሳውስትና ዲያቆናት በሚስቶቻቸው ምክንያት ለስብከተ ወንጌል እንደማይፋጠኑ መናገራቸው ትክክል አይደለም።

መጻሕፍትን አተኩረው ለማይመለከቱ ሰዎች ካልሆነ በስተቀር እንደዚህ ያለው አስተሳሰብ በማንም ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም ለምሳሌ በሐዋርያት ጊዜ የነበሩት ቅዱሳት አንስት ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል እንጂ ለወንጌል ትምህርት እንቅፋት ሆኑ የሚል ጽሑፍ አይገኝም ቅዱስ ጴጥሮስን ሩዴ የምትባል ሴት ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት ረድታዋለች ለሐዋርያው ጳውሎስም ፌቤን ተብላ የምትጠራ አንዲት ሴት መልእክቱን ወደ ሰዎች በማድረስ አገልግላዋለች እንዲሁም ከሰብአ አርድእት መካከል ብዙዎቹ ባለሚስቶችና ባለትዳሮች እንደነበሩ ሲታወቅ ሚስቶቻቸው እንቅፋቶች ስለሆኑባቸው ወንጌልን አልሰበኩም አላስተማሩም የሚል ጽሑፍ የለም እንዲያውም ወንጌል ከጽንፍ እስከ ጽንፍ የተሰበከችው በእነርሱ ጊዜ ነው ።

በዚህ አንጻር ቀሳውስትና ዲያቆናት ለስብከተ ወንጌል ሲሰለፉ ሚስቶቻቸው እየረዷቸው ወንጌል በብዛት እንዲሰራጭ ሆኗል እንጂ እነርሱ ለባሎቻቸው እንቅፋቶች በመሆን የወንጌል ትምህርት ወደ ኋላ እንዲጎተት አያደርጉም ። የወንጌል ቃል የሚስፋፋው በመረዳዳት እንጂ በብቸኝነት አይደለምና ።

በዘመነ ሐዋርያት ከሐዋርያት ጋር ከነበሩት ቅዱሳት አንስት አንዳንዶቹ ሐዋርያት ሲያስተምሩ ውለው የሚመገቡትን ሲያዘጋጁ አንዳንዶቹ ደግሞ ወንጌልን ያስተምሩ ነበር ይህም በማርያምና በማርታ ሊታወቅ ይችላል ማርያምና ማርታ እህትማማቾች ነበሩ ግን ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት አገልግሎት በተለያየ መንገድ ነበር ማርያም ከሐዋርያት ጋር ወንጌልን የምታስተምርና የምትማር ስትሆን እህቷ ማርታ ግን ሐዋርያት የሚመገቡትን በማዘጋጀት ብዙ ትደክም ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን ማርታ ወደ ጌታችን ወደ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀረብ ብላ «ጌታዬ ሆይ እህቴ ብቻዬን ስትተወኝ አላሳዝንህምን እባክህን እህቴን ማርያምን እርዷት በላት ብላ ለመነችው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልሶ ማርታ ሆይ ! ብዙ ነገርን በማዘጋጀት ብዙ ጊዜ ትደክሚያለሽ ነገር ግን ጥቂት ይበቃሻል ማርያም ግን ወንበዴዎች የማይቀሟትን ሌቦች የማይሠርቋትን ትምህርት መረጠች» በማለት አስረድቶቷል ሉቃስ 10፡ 39 - 42።

ይህ የተጠቀሰው ቃል የሚያመለክተው ለወንጌል መስፋፋት ከትምህርት ጋር ሥራም አብሮ ተዳምሮ የሚቆጠር እጅግ በጣም ተፈላጊ መሆኑንና ሕጋውያን ቀሳውስትና ዲያቆናትም ከሌሎች ክፍሎች የበለጠ አገልግሎት የሚያበረክቱ መሆናቸውን ነው ባሎቻቸው ወንጌልን ለማስተማር ሲሰለፉ ሚስቶቻቸው ሲያስተምሩ ውለው የሚመገቡትን በማዘጋጀት ይረዷቸዋል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልዕክቱ ላይ ከብቸኞች አስተማሪዎች በይበልጥ ሚስቶች ያሏቸው ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ማበርከታቸውን ሲያስረዳው » እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ ቄስ አስተማሪ እንዲህ ሊሆን ይገባል የማይነቀፍ የአንዲት ሚስት ባል ልከኛ ራሱን የሚገዛ እንደሚገባው የሚሠራ እንግዳን ተቀባይ ለማስተማር የበቃ የነቃ የማይሰክር የማይጨቃጨቅ ገር የሆነ በሆነ ባልሆነ ነገር የማይከራከር የዚህ ዓለምን ገንዘብ የማይወድ ልጆቹን ሥርቶ ቀጥቶ የሚያሳድግ ቤቱን በመልካም የሚያስተዳድር ሰው መሆን አለበት የራሱን ቤተ ሰብእ በመልካም የማያስተዳድር ከሆነ ግን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንን ያስተዳድራል ብለው አምነው እንዴት ይሾሙታል?» በማለት ጽፎለታል 1ኛ ጢሞ 3.2 ። በተጨማሪም ይህ ሐዋርያ ሕዝብን መስ

ወደገጽ ፲፪ ዞሯል



# ጥምቀት በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት

**ጥምቀት በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት**

በብሉይ ኪዳን ጥምቀት በውሃ መታጠብ ፤ መጥለቅና መንፃት ፤ ነበር ፡ በብሉይ ኪዳን በዓል ሲከበር በዓሉን ለማክበር የሚሰበሰበው በውሃ በመረጨት ፡ (በመጠመቅ) ለበዓሉ ዝግጅት የሚፈለጉ ዕቃዎች ሁሉ በውሃ መታጠብና መንጻት ነበረባቸው ። ዘሌዋ. 6 ፡ 27 ።

በብሉይ ኪዳን ሰውን ወይም ዕቃን ያረክሳሉ ተብለው የሚታመንባቸው ነገሮች ነበሩ ለምሳሌ ለመሥዋዕት የታረዱትን ጊደር ደም በጣቱ የነካ የዝግባ ዕንጨትና ግምጃ ወስዶ የጊደሪቱ ሥጋና አጥንት በሚቃጠልበት የጣለ ካህን ልብሱንና ገላውን በውሃ ካልታጠበ ወደ ሰፈር መግባት አይፈቀድለትም ነበር ። የሞተ ሰው አስከሬን የነካ ፡ ሰው በሞተበት ድንኳን ውስጥ የገባ ሁሉ እንደ ርኩስ ይቆጠር ስለነበር በውሃ መታጠብና (በመረጨትና) መንጻት የተለመደ ሕግ ነበር ዘኁ 19 ፡ 18 ፡ መዝ. 50 51 ፡ 7 ።

ከብሉይ ኪዳን እምነት ውጭ የነበረ ሰው የኦሪትን እምነት ሲቀበል ከማኅበረ አይሁድ ከመግባቱ በፊት መገረዝና መታጠብ ግድ ነበር ። ከተገረዘና ከተጠመቀ በኋላ እንደ አይሁድ ሥርዓት መባእ ማቅረብና ከማኅበሩ ጋር አንድ መሆን ይፈቀድለታል ፡ ከሌላው እምነት ወደ ይሁዲነት ሲገባ ዕለት እንደ ተወለደ ሕፃን ይቆጠራል ። ራሱን ከኢግዙርነት መለየት ከመቃብር እንደ መውጣት ነው ተብሎም ይታመን ነበር ።

ከዚህም ሌላ በሙት ባሕር አካባቢ ቁምራን በተባለው ገዳም ይኖሩ የነበሩት "ኤሲየንስ" (ናዝራውያን ማለት ይመስላል) የተባሉ ወገኖች ከአይሁድ ጥምቀት ለየት ያለ ጥምቀት እንደ ነበራቸው ይነገራል ፤ የማንኛውም እምነት ተከታይ ቢሆን ወደ እነርሱ ማኅበር መግባት የሚፈልገውን ሁሉ አጥምቀው ይቀበሉት ነበር ፤ እንዲሁም ኢግብረ ገቦችንና ሕሙማንን የመንጻት ጥምቀት ያጠምቁ እንደ ነበረ ከታሪክ መረዳት ይቻላል ። በተጨማሪም ሰዎች ሲጋቡና የመጀመሪያ ልጃቸውን ሲወልዱ ያጠምቁ ነበር (መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን 2 ፡ 8 - 12)

ሌላው የብሉይ ኪዳን ጥምቀት የዮሐንስ ነው የዮሐንስ የንስሐ ጥምቀት አጠመቀ ማር 1 ፡ 4 የዮሐንስ ጥምቀት አማኞችን ለክርስቶስ ጥምቀት የሚያዘጋጅ የክርስቶስን ጥምቀት ለመቀበልና በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ባለቦታ ለመሆን የሚያበቃ ነበር ። የዮሐንስ ጥምቀት ሁለት ነገሮችን ያመለክታል።

1ኛ ከኃጢአት ወደ ሥርየት ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር መመለስን ።

2ኛ ሥርየተ ኃጢአትን አግኝቶ ከማኅበረ ጻድቃን ጋር አንድ መሆንን ያሳያል ።

በብሉይ ኪዳን ነቢይ ወይም መሢሕ ወደዓለም ይመጣል ። ሰዎችንም ያድናል ተብሎ ተነግሮአል ።

ከመሢሑ መምጣት አስቀድሞ ግን አዋጅ ነጋሪና መንገድ ጠራጊ ኤልያስ ይመጣል ተብሎ ስለ ዮሐንስ መጥምቅ ተነግሮ ነበር ። እርሱም በመጣ ጊዜ ለክርስቶስ ጥምቀት የሚያበቃ የንስሐ ጥምቀት እንደሚያጠምቅ ተጽፎአል ። ሚል 3 ፡ 1 - 3 ዮሐ፡1 ፡ 25 በብሉይ ኪዳን ይፈጸም የነበረው ጥምቀት በሐዲስ ኪዳን እንደሚፈጸመው ጥምቀት ምሥጢር አልነበረም የብሉይ ኪዳን ጥምቀት የመንፃት ጥምቀት ነበር ዮሐ 2 ፡ 6 ።

የሐዲስ ኪዳን ጥምቀት በማዳን ሥራ የተመሠረተ ነው ፤ ክርስቶስ የመጣው ለማዳን ነው ጥምቀትንም የሠራው ከእግዚአብሔር ርቆ የነበረውን ሰው ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብና የእግዚአብሔር ልጅ ለማድረግ ነው መድኃኒታችን ክርስቶስ ጥምቀት የማያስፈልገው ጻድቅ ሲሆን በኃጢአት ምክንያት አድፎ የነበረውን የሰው ልጆች ጽድቅ ለማደስና በእርሱ ጥምቀት የሰዎችን ጥምቀት ለመቀደስ ተጠመቀ ። ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ ከሰማያት በተሰማው ድምፅ የክርስቶስ አዳኝነት የጥምቀት መስተሥርይነት ተረጋገጠ ።

የሐዲስ ኪዳን ጥምቀት በውሃ ብቻ አይደለም በመንፈስ ቅዱስም ነው እንጂ የመንጻት ብቻም አይደለም ። ልጅነትንም የሚያስጥ እንጂ የሐዲስ ኪዳን ጥምቀት አላማ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን የበደል መጋረጃ ለማስወገድ ሰውና እግዚአብሔርን ለማቀራረብ ነው ። የሐዲስ ኪዳን ጥምቀት ሰዎችን የእግዚየብሔር የጸጋ ልጆች ያደርጋል ። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ያቀርባል ። እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆንና መንግሥቱን ለመውረስ ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ መወለድ ያስፈልጋል ዮሐ. 3 ፡ 5 ።

የብሉይ ኪዳን ጥምቀት መሥራቾች ለራሳቸው መዳን ፤ መንጻትና መቀደስ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ነበሩ ። የሐዲስ ኪዳን ጥምቀት መሥራች ግን ደኅንነትን የማይሻ ራሱ አዳኝ ፡ መንጻትንና መቀደስን የማይሻ በባሕርዩ ንጹሕና ቅዱስ የባሕርይ አምላክ ክርስቶስ ነው ። በጥምቀቱ የሰዎችን ጥምቀት ቀደሰ ፤ ለጥምቀት ኃይልን ሰጠ ። በብሉይ ኪዳን ጥምቀት የተጠመቁ ሁሉ ከበደልና ከፍዳ ለመዳን አልቻሉም ነበር በሐዲስ ኪዳን ጥምቀት የተጠመቁና የሚጠመቁ ግን ከቀደመው የበደል ኃጢአት ድነው የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ሥልጣን አላቸው ።

ኦሪት ለወንጌል አምሳልና መርገፍ ነበረች ፤ ወይም ወንጌል በኦሪት ተሰውራ ስትኖር ጊዜው ሲደርስ ኦሪት በወንጌል ተገልጠች ተተረጐመች ። እንዲሁም የሐዲስ ኪዳን ጥምቀት በብሉይ ኪ

ወደ ገጽ ፲፪ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## ክርስቲያናዊ ጋብቻ

ጋብቻ በግብረ ገብነት በፍቅረ እግዚ
አብሔር በፍቅረ ሀገርና በፍቅረ ሰብእ
የተጌጠ ሲሆን እጅግ መልካም ነው። ያለ
ፍቅረ እግዚአብሔር የሚፈጸም ጋብቻ
በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል ፍቅርን አ
ይመሠርትም ። ፍቅረ ሀገር የለበትም
ጋብቻ እንደዚሁ ነው። ከዚሁም ሁሉ
ጋር በሁለቱ መካከል እውነተኛ ፍቅር
ያስፈልጋል። እውነተኛ ፍቅር ካላቸው
እግዚአብሔር በመካከላቸው ይኖራል።
«ጋብቻ 3 እግሮች እንዳሉት ባርጩሜ
ወንበር ነው » ይባላል 1ኛው እግር ልጅ
መውለድ ነው፣ 2ኛው እግር እርስ በርስ
መረዳዳት ነው። 3ኛው ፍቅር ነው ።
ታዲያ ከሦስቱ ሁለቱ ልጅ መውለድና
መረዳዳት የተባሉት እግሮች ቢሰበሩ ጋ
ብቻ አይወድቅም። አይፈርስም። ግን
ሦስተኛው ፍቅር የተባለው እግሩ ቢሰ
በር ጋብቻ ይወድቃል ይሰበራል። በዚ
ህም መሠረት በተጋቢዎቹ ሁሉ መካከ
ል ፍቅር ተቀዳሚ ነገር መሆኑን እናስ
ታውሳለን።

በዚህ ርእስ ለመጻፍ የፈለግነው ስለ
ፍቅር ሳይሆን በእውነተኛ መንፈሳዊ ፍ
ቅር ስለተፈጸመው ስለ ወይዘሪት ዓለሚቱ
ምትኩና መምህር ኢ.ሞ ገቦ ጋብቻ ነው።
የወ ት ዓለሚቱና የመምህር ኢ.ሞ ሥር
ዓተ ጋብቻ የተፈጸመው ጥቅምት 9 ቀን
1973 ዓ.ም. በጐሬ ደብረ ገነት ቅድስት
ማርያም ቤተ ክርስቲያን ነው ሥርዐተ
ተክሊሉንም የፈጸሙላቸው የኢሉባቡር
ሀገረ ስብከት ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ
ናቸው።

ወ/ት ዓለሚቱ ምትኩ በጐሬ ገነት ቅ
ድስት ማርያም የመንፈሳውያን ወጣቶች
ማኅበር አባል ሆና ለብዙ ዓመታት ፡ መ
ጽሐፍ ቅዱስ በመማር በማስተማር ና
በመዘመር መንፈሳዊ ሕይወትዋንና ግ
ብረገብነትዋን የገነባች መንፈሳዊት ወ
ጣት መሆንዋ ጋብቻዋን በሥርዐተ ተክ
ሊልና በቅዱስ ቁርባን በመፈጸምዋ ተመ
ስክሮአል።

ወ ት ዓለሚቱ በአሁኑ ጊዜ መምህርት
ናት። መምህርት ዓለሚቱ በመንፈሳዊ
ውም ሆነ በሥጋዊው ትምህርት የማስ
ተማር ልምምድ ስላላት ወደፊት ለምታ
ፈራቸው ልጆች እጅግ መልካም አርአ
ያና ምሳሌ እንደምትሆን እናምናለን።
ከዚያም በፊት በትምህርት ቤት ለምታ
ስተምራቸው ልጆች ሁሉ እውነተኛ ም
ሳሌ ናት።

መምህርት ዓለሚቱና መምህር ኢ.ሞ
በጥምቀት ከእግዚአብሔርና ከማኅበረ
ቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ የሆኑባትን
ዛሬም በተክሊልና በቁርባን አንድ አካል
አንድ ሥጋ የተባሉባትን ቤተ ክርስ
ቲያን እስከ መጨረሻ ሕይወታቸው
እንዲያገለግሉዋት ከሥርዓትዋና ከሕግዋ
እንዳይወጡ በዚህ አጋጣሚ ክርስቲያና
ዊ ምክራችንን እናስተላልፋለን።



መምህርት ዓለሚቱና መ/ ኢ.ሞ ጋብቻቸውን በቤ/ ክርስቲያን በፈጸሙበት ወቅት

## ታቦትና ክብሩ ..

ከገጽ ፺ የዞረ

ዳር ድንኳን እየተከሉ ዳስ እየጣሉ ከ
ዚያ እየተሰበሰቡ ማክበር በዓሉን በእው
ነተኛ ታሪካዊ መልኩ ለማሰብ ነው ።
በመጀመሪያው ሥርዓት ኢያሱና ሕ
ዝቡ ካህናቱ ከዮርዳኖስ ወንዝ ዳር ታ
ቦተ እግዚአብሔርን ይዘው አድረው
ዮርዳኖስን ከፍለው ተሻግረውበታል
በሁለተኛው ሥርዓት በታቦት ላይ
አድሮ ሕዝቡን የመራው አምላክ ሰው
ሆኖ ሥጋ ለብሶ ከሰዎች እንዳንዱ ሆኖ
በዮርዳኖስ ተጠምቆ ሕዝቡን ወደ ር
ስተ መንግሥተ ሰማያት አግብቶበ
ታል ። በዚህ ምክንያት በየዓመቱ ምእ
መናንና ካህናቱ ታቦተ እግዚአብሔርን
ይዘው ወደ ወንዝ ወርደው ክብር የማይ
ሻው አምላክ እነሱን መስሎ የፈጸመላ
ቸውን ቸርነት በጥምቀት የሰጣቸውን
ጸጋና ሕይወት እያሰቡ ዘጠናዘጠኙን
ነገድ ትቶ ወደ ባሕር - ገብቶ ቆመ ።
በሰላም ገባ በሰላም ወጣ ። ሰማያዊው

ወይ. ጽ፥ ገጽ ዞሯል

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ምቀት ከሥላሴ መወለድ ማለት ነው ፡
በጥምቀት ከሥላሴ ያልተወለደ ሰው
ግን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማ
የት አይችልም ።

✻ ✼ ✲

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ሦስት አብያተ ክርስቲያናት በአንድ
ላይ የሰበካ ጉባኤ ለማቋቋም አስበው መ
ነጋገር ጀምረው ነበር ግን በመካከል አ
ንዳንድ ችግር እያጋጠማቸው ነው ችግ
ሩ፡፡-

1ኛ አንደኛው ቤተክርስቲያን ደብ
ር ስለሆነ ለካህናት አበል በዓመት ብር
420 አራት መቶ ሃያ ብር ያገኛል ሌ
ላው ገጠር ስለሆነ ሃምሳ ብር ያገኛል
ይሁን እንጂ በጸበልና በስእለት ብዙ
ገቢ ይገኛል ። ስለዚህ ደብሩም ከነ አራ
ት መቶ ሃያ ብር ገጠሩም ከነስእለቱ ከ
አንድ ላይ ይሁን ሲባል ባለ አራት መቶ
ብሮች 420 ብርን ወደ አንድነት አናስገ
ባም ይላሉ ከዚህ ላይ ባለስእለቶችም
እንግዲያውስ እኛም ከስእለትና ከጸበል
የሚገኘውን ለግላችን እናደርጋለን
በማለት ይለያያሉ ።

2ኛ አንዱ ብዙ አፀድ አለው ሌላው
የለውም አጸድ የሌለው ቤተ ክርስቲያ
ን በሚታደስበት ጊዜ አጸድ እንቁረጥ
እናስቆርጥም መባባልም ሁለተኛው
ችግር ነው ።

3ኛ አንዱ በመጽሐፍት የበለጸገ ነ
ው ሌላው የለውም ታዲያ በሰበካ ጉባ
ኤ አንድ ከሆንን መጻሕፍቱን አካፍሉ
ን ፡ አናካፍልም በመባባል በአንድ የሰ
በካ ጉባኤ ለመደራጀት ችግር ገጥሞአ
ቸዋል ። ለዚህ ችግር መፍትሔ የሚሆ
ን አስተያየት ከትንሣኤ እናገኛለን ብለ
ን ተስፋ እናደርጋለን ።

መ እስጢፋኖስ ዋጋዬ
ጐንደር ሀገረ ስብከት
የሰበካ ጉባኤ ኃላፊ

● መ እስጢፋኖስ ዋጋዬ ስለ ጥያቄዎ
እጅግ እናመሰግናለን ። በሰበካ ጉባኤ
አንድ የሆኑ የአንድ አካባቢ አብያተ
ክርስቲያናት በማንኛውም ሀብት ስለመ
ተባበር ጉዳይ በቃለ ዐዋዲው ምዕራፍ
5 አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል
ለ- በተጻፈው መሠረት መመሪያ አስ
ፈላጊ ይመስለናል ። ቃለ ዐዋዲውም
ስለዚህ ያለው ሙሉ ቃል ይህ ነው “ለ”
በወረዳው ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ አስ
ተዳደር ውስጥ በአንድይድ አካባቢ የሚ
ገኙ የተቀራረቡ የአጥቢያ አብያተ ክር
ስቲያናት ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያ
ት አንድ ላይ ሆነው በሀብትም ሆነ በአ
ገልግሎት መረዳዳት መተባበር ቢፈልጉ
ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጠቅላላ አቋ
ማቸውና ሁኔታቸው በሚገባ እየተጠና
አቋማቸው ተጠብቆ በአንድነት ተደራ
ጅተው መሥራት ይችላሉ ።

ስለሁለተኛው ጥያቄዎ የምንሰጠው
አስተያየት እንዲህ ነው በመሠረቱ ዐፀድ
የቤተ ክርስቲያን ቅርስ ነው ። ቅርስነ
ቱም ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳ
ይሆን ለሁሉም ነው ። ከዚህም የተነሣ
ከፍተኛ ጥንቃቄና እንክብካቤ ሊደረግ
ለት ይገባል ። አብያተ ክርስቲያናት
በታነፁ ወይም በታደሱ ጊዜ ሊቆረጥ የ
ሚገባው የዐፀዱ ቅርስነት በማይጠፋ ሁ
ኔታ ማለት ቤተ ክርስቲያኑ እንዳይራቆ
ት እየታየ መሆን አለበት ። ከዚህም ጋ
ር በምትኩ አዲስ ችግኝ መትከል ያስፈ
ልጋል ። በሌላም በኩል በሰበካ ጉባኤ
አንድ ከሆን በማለት የአንዱን ቤ ክ
ዐፀድ መመንጠር አግባብ አይደለም ።
ቤተ ክርስቲያንን ከማራቆት ይልቅ ከሕ
ብረቱ ገንዘብ በማውጣት ከውጭ እን
ጨት መግዛት ይሻላል ። ይህም ሲሆን
የተባበሩት የሰበካ ጉባኤ አባላት ገንዘ
ብ አውጥቶ እንጨት ከመግዛትና የቤተክ
ርስቲያኑን ዐፀድ ከመቁረጥ የትኛው እን
ደሚሻል በመመካከር ሊያደርጉት ይቻ
ላል ።

በ3ኛው ጥያቄ ላይ የጠቀሙት ደግ
ሞ የመጽሐፍ ጉዳይ ነው ። ለአንደኛው
ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት በብዛት ቢኖ





www.ethiopianorthodox.org

ሩት በንብረትነት ለሌላው ያካፍል ማለ ት በቂ ሃሳብ አይደለም ። ግን በአገልግ ሎት ጊዜ ብዙ መጻሕፍት ያሉበት ደብ ር ካህናት መጻሕፍቱን ይዘው መጥተ ው ሲያገለግሉ መዋል ይችላሉ ለምሳሌ በፍትሕት ጊዜ መጽሐፈ ግንዘቱን ፀሁ ርግጊዜ መጽሐፈ ተክሊሉን በበዓል ቀን ለተሰበሰቡት ሕዝብ የሚነበበውን ድር ሳን ወይም ገድልና ተአምር ከአንዱ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላው ቤተ ክርስቲያን ወስደው ሲያስተምሩበት ውለው መመ ለስ ተገቢ ነው እንላለን ። ከዚህም ሌላ ትንሣኤ አንድ ግላዊ አስተያየት ለመስ ጠት ይፈልጋል መ/እስጢፋኖስ ዋጋዬ እርስዎ እንደጠቀሱት ሁሉ በሰበካ ጉባ ኤ የተባበሩ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አንድ ማዕከላዊ ቤተ መጻሕፍት አዘጋ ጅተው ከዚህ በፊት የነበራቸውንና ዛሬ ም ሆነ ወደፊት ልዩ ልዩ መንፈሳውያን መጻሕፍትን እየገዙና እያሰጻፉ በክብር ቢ ጠብቁ መልካም ነው ። ከዚያ ሁሉም እ ንደ ፍላጐታቸው ከቤተ መጻሕፍቱ በ ሥነ ሥርዐት እያወጡ መጠቀም ይች ላሉ ።

* **

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

አዲስ አበባ

የእኔ ምኞት ምሥጢር አይቼ ለመቀ ደስ ነበር ። ግን ይህ ምኞቴ ሳይፈጸምል ኝ ቀረ ። ምክንያቱም ሚስት አግብቼ በ አንዳንድ አለመግባባት ተፋታን ። አሁን ሌላ ሚስት አግብቼ እኖራለሁ ። በመ ሥረቱ ከወላጆቼ ተለይቼ በጥሬ ልመና የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ተምሬ ነበ ር። ስለዚህ አሁን ካለችው ሚስቴ ጋር ቆርቤ ምሥጢር አይቼ ፥እንዳላስቀድስ የሚከለክለኝ ሕግ ይኖራል ? ወይስ ይ ፈቀድልኛል ? መልሱን በጉጉት እጠባ በቃለሁ ።

የ፶ አለቃ ሀብተ ገብርኤል ጉልማ

አ.አ

• የ፶ አለቃ ሀብተ ገብርኤል ጉልማ ያቀረቡትን ጥያቄ ተመልክተነዋል እ ንድ አማኝ ከሁሉ አስቀድሞ የሚከተለ ውን እምነት መረዳት አባል የሆነበትን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ እምነትና የም ሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን አፈጻጸም ለይቶ ማወቅ ይኖርበታል ፤ የእርስዎ ምኞት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን አውቀው በቅስና ለማገልገል ሆኖ ሳለ በጋብቻ መደገም ምክንያት ቅስና ለመ ቀበል ባይችሉም ምሥጢራተ ቤተ ክ ርስቲያንን አውቀው " ይበሉ ሕዝብ " የሚለውን ተሰጥዎ እየተቀበሉ ከማስ ቀደስና ከመቁረብ የሚከለክል ሕግ የ ለም ።

---

## ጥምቀት በብሉይና ...

ከገጽ ፱ የዞረ

ዳን ጥምቀት አምሳልነት ከቆየ በኋላ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ልጅነትን በማሰ ጠት ተገለጠ።

የብሉይ ኪዳን ጥምቀት የተለያየ ይዘት ነበረው የሐዲስ ኪዳን ጥምቀት ግን ይዘቱ አንድ ነው ፤ ይኸውም ልጅነትን ማስጠትና በሦስቱ ስም በውሃ መጠመ ቅ በሚሮን መታተም ነው ፤ ሦስቱን አ ካላት ማለት አብ ወልድና መንፈስ ቅ ዱስን አንድ አምላክ እንደሆኑ አምኖ መጠመቅ ከዚያ በኋላ ጥምቀት የማይ ከለስና የማይደገም አንድ ብቻ መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል ። አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት ፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠ ራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁ ሉም አባት አለ" ። ኤፌ. 4፥5 ።

የብሉይ ኪዳን አማኞች በውሃ ብቻ ተጠምቀውና መንፈስ ረድኤትን ተቀ ብለው ከማኅበረ አይሁድ ጋር አንድ መሆንን ይታደሉ ነበር ። የሐዲስ ኪዳን አማኞች ግን በውሃና በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀው መንፈሳዊ ልደትን በጸጋ ከእግዚአብሔር ይወለዳሉ ከማዕሠረ ኃጢአት ይፈታሉ ። ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ይሆናሉ ። በክርስቶስ ክርስ ቲያን በወልድ ውሉድ ይባላሉ ።

ራድ አስረስ

---

## ለስብከተ ወንጌል ...

ከገጽ ፰ የዞረ

ሎ ማስተማር ውጤቱ ክፍ ያለ መሆኑን ራሱን ምሳሌ በማድረግ ሲናገር "ነገር ግን እኔ ከሰው ሁሉ አርነት የወጣሁ ስሆ ን ራሴን ለሁሉ አስገዛለሁ ሁሉን እረባ ዘ ንድ ከአይሁድ ጋር እንደአይሁዳዊ ሆንሁ አይሁድን እረባ ዘንድ ከኦሪት በታች ካሉት ጋር ደግሞ ከኦሪት በታች እንዳ ለሁ ሆንሁ ከኦሪት በታች ያሉትን እረ ባዘንድ ሕግ ከሌላቸው ጋር ሕግ እንደ ሌለኝ ሆንሁ ሕግ የሌላቸውን ረባ ዘንድ ከደካሞች ጋር እንደ ደካማ ሆንሁ ከር ሳቸውም ሰዎችን ፈጽሜ አድን ዘንድ" ብሏል 1ኛ ቆሮ.9፥19-22 ።

ይህንና ይህንን የመሳሰሉትን አስተው ለን ስንመለከት በብቸኝነት ተሰልፈው ከሚያስተምሩ መነኮሳትና ባሕታውያን ይልቅ ሚስት አግብተው በትዳር ተወስ ነው በሕዝብ መካከል እየተገኙ የሚያስ ተምሩ ቀሳውስትና ዲያቆናት የበለጠ አስተዋጽኦ ለማበርከት የሚችሉ መሆ ናቸውን እንገነዘባለን ።

ለስብከተ ወንጌል መስፋፋትም የሚ ፋጠኑ ከሕጋውያን ቀሳውስትና ዲያቆቆ ናት ይልቅ ሌሎች ክፍሎች አሉ ብለን እንገምትም ከኑሮ ጓደኞቻቸው ጋር ተባብረው የመሥራት መልካም ፍላጐ ት አላቸውና ።

ቄስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ

X X



---

## የሃይማኖት ዐምድ

«ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፥ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፡፫) ።

## ምሥጢረ ቁርባን

ምሥጢረ ቁርባን ከክርስቶስ ጋር አን ድ የምንሆንበት የርሱን ሕይወት ተዋ ሕደን አዲስ ፍጥረትን የምንሆንበት የክ ርስቶስን ሕማሙን ሞቱን ማለትም ለእ ኛ ሲል የተቀበለውን መከራ መስቀል የምናስብበት አዲስ ሥርዓት ነው። የዚ ህም ምሥጢረ ሥርዓት በጉልህ የታየው ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሊሠራው ያቀደ ውን ዋና ተግባር በማገባደድ ወደ ፍጻ ሜ ሲደርስ በዕለተ ሐሙስ ከደቀ መዛ ሙርቱ ጋር ባደረገው የመጨረሻ ራት ላይ ኅብስቱን አንስቶ በጸሎት ከባረከ በኋላ «ንሡ ብሉ ይህ ሥጋየ ነው» አለ ጽዋውንም እንዲሁ ካመሰገነ በኋላ ሲ ሰጣቸው ሁላችሁ ከዚሁ ጠጡ ይህም ለብዙዎች የኃጢአት ማስተሰረያ ይቅ ርታ ማግኛ ይሆን ዘንድ የሚፈስ የአዲ ስ ኪዳን ደሜ ነው። በማለት አማናዊነ ቱን አስረድቶአል።

ከዚህም ሁሉ ጋር«የሕይወት እንጀ ራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራ ብም ፤ በእኔ የሚያምንም ሁሉ ከቶ አይ ጠማም ዮሐ.6.35 » ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ማንም ሰው አምኖ ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይ ኖራል እኔም ስለዓለም ሕይወት የምሰ ጠው እንጀራ ሌላ ሳይሆን ራሱ ሥጋዬ ነው» /ዮሐ 6.51./» ዕውነት ዕውነት እላችሁዋለሁ የሰው ልጅ ተብሎ የሚጠ ራውን የክርስቶስ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙ ንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት አይኖራችሁም ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ እርሱ ብቻ የዘላለም ሕይወት ይኖረዋል፤እኔም በመጨረሻው ቀን ከሞ ት አስነሣዋለሁ።ሥጋዬ እውነተኛ ምግብ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና ።ሥጋ ዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ እርሱ በእኔ ሕያው ሆኖ ይኖራል እኔም በር ሱ እኖራለሁ ። ቁ/53 - 56 በማለት የክርስቶስ ሥጋና ደም ከምድራዊ ምግ ብና መጠጥ የተለየ አዲስ ሕይወት የሚ ሰጥና አማኞች ከርሱ ጋር የሚኖሩቸውን ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚሰጥ መሆኑን በአማናዊ ቃሉ አረጋግጠዋል።

### የአገልግሎቱ አፈጻጸም

ምሥጢረ ቁርባን በካህናት የጸሎት አገልግሎት የሚፈጸምና በእግዚአብሔ ር ቃል የሚከብር ምሥጢር ነው። አገል ግሎቱም የሚፈጸመው ለሚያምኑ ብቻ ነው። የምሥጢረ ቁርባን አገልግሎት የሚታይ ቢሆንም የማይታይ ልዩ ጸጋ አለው። ይኸውም ኅብስቱ በሃሕል ወይ ኑ በዕዋ ሆኖ ካህኑ ሲጸልይበትና ሲባር ከው በእግዚአብሔርም ቃል ሲያከብረው አማኞችም የጸሎት ተባባሪዎች በመሆን አሜን ይሁንልን ይደረግልን በማለት በመማጠን ድጅ ሲጠኑ አብረው ም ተሰ ጥዎ በመቀበል ሲዘምሩ ይታያሉ ይሰማ ሉ። ከዚህም የተነሣ ይህ የሚታይ አገል ግሎት ተብሎ ይጠራል ኅብስቱ ተለው ጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር በመሆን ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኮት በመሆን ለሚቀበሉት አማኞች ሁሉ የዘለዓለም ሕይወትን ሲሰጥ ግን ከቶ አይታይም አይታወቅም ይህም የማይታይ ጸጋ የተባለበት ምክኒያት ይኸው ነው።

ይሁን እንጂ እነዚህ አገልግሎቶች ሁ ለቱም ተፈጻሚነት ያላቸው መሆኑን አ ምኖ መቀበል ይገባል። ያለ እፍአዊ አገ ልግሎት ውስጣዊ አገልግሎት ሊፈጸ ምና ጸጋውም ሊሰጥ አይችልምና ነው።

### የኅብስቱና ወይኑ አለዋወጥ

የምናቀርበው ኅብስትና ወይን በእግ ዚአብሔር ቃል /በጸሎት/ ተለውጦ ሥጋ አምላክ ደመ አምላክ ይሆናል ብለን እና ምናለን ይህንም ራሱ ክርስቶስ ይህ ህብ ስት ሥጋዬ ነው ይህም ወይን ደሜ ነው ሲል በተናገረው ቃል መረዳት ይቻላል ስለዚህም ሥጋውን ደሙን በተቀበልን በቆረብን/ ጊዜ በዕርግጥ የክርስቶስ ሥጋ ና ደም ነው ብለን አምነን እንቀበለዋለን እንጂ እንደሌሎች ምሳሌ ነው ማለት አይገባንም ። ደግሞም በምንቀበልበት ጊዜ በተለይ እንደ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖታችን ሕግና ሥርዓት ሥጋው ንም ደሙንም በአንድነት እንቀበላለን እንጂ አንዱን ከሌላው ለይተን ነጥለን መተው አይገባም ቅደም ተከተሉም ቢ ሆን ልክ ክርስቶስ በጸሎተ ሐሙስ እንዳ ቀረበው መጀመሪያ ቅዱስ ሥጋው ቀጥ ሎም ክቡር ደሙ ይቀርባል።

ይህም ዘለዓለማዊ ሕይወተ ሥጋን ሕይወተ ነፍስን ለማግኘት የሚያስችለ ን ፍጹም የክርስቶስ ሥጋና ደም መሆኑን ለማመን ከቅዱስ ቃሉ መረዳት ይኖርብ ናል እንደተራ ኅብስት ቆጥረነው ብንጠ ራጠር ግን በደህንነት ፈንታ መቅሰፍ ትን መጋበዝ ይሆንብናል። ይህንም ሐ ዋርያው ጳውሎስ ሲያስገነዝብ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ወይ ኑም ተለውጦ ደመ ወልደ እግዚአብሔ ር መሆኑን ሳያምንና ይህኑ በእግዚአብ ሔር ቃል ሳያረጋግጥ በመጠራጠር የሚ ቀበል ሰው ቢኖር«ደይኖ ወመቅሠፍቶ በልዐ» የዘላለም ጥፋትንና መቅሠፍትን ይቀበላል በማለት አስጠንቅቋል። 1ኛ ቆሮ. 11፥27

በዕርግጥ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ አም ላክ ወይኑም ተለውጦ ደመ አምላክ ይሆ ናል ስንል በዓይነ ሥጋ ስናየውና በዕደ ሥጋ ስንዳስሰው በአምሳለ ኅብስትና ወይን አይታይም ማለታችን አይደለም ነገር ግን እግዚአብሔር ሥልጣን በሰጠ ው ካህን ጸሎት በእግዚአብሔር ቃል

ወደ ገጽ ፲፯ የዞረ



www.ethiopianorthodox.org

# ይህን ያውቁ ኖረዋል ?

እጅጉ ረታ

መጽሐፍ ቅዱስ የሳይንስ ወይም የፍልስፍና ትምህርት መማሪያ መጽሐፍ እንዲሆን፣ ቀድሞ ውኑ ሆን ተብሎ የተዘጋጀ መጽሐፍ አይደለም። ባለመሆኑም ስለ አንዳንዱ የሳይንስ ክፍል ጥናትና ምርምር ውጤቶች ዝርዝር ነገሮችን አይተነትንም ። የሳይንስ ጥናትና ምርምር ም ስለ ጽድቅና ኩነኔ ወይም ከሞት መጋረጃ በስቲያ ስላለው ሕይወት የሚናገረው አንዳችም ነገር የሌምየተጠናቀቀም ዝርዝር መግለጫ አያቀርብም ። ግን ከዘመናት በኋላ ፣ እያደገ፣ እየተሻሻለ የመጣው የሳይንስ ጥናትና ምርምር ውጤት፣ ከዘመናት በፊት በእግዚአብሔር መንፈስ በተጻፈው በቅዱስ መጽሐፍ የተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል የማይሳሳት እውነት መሆኑን አረጋግጧል ።

በማረጋገጥም ላይ ነው። በዚህም ሳይንስና የሳይንስ ውጤቶች ለመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ትክክለኛነት ዓይነተኛ ምስክር ወይም ማስረጃ ናቸው ለማለት ይቻላል። በመሠረቱ ይህ ያለንበት ዘመን ከመቸውም ጊዜይልቅ እውቀት የበዛበት ዘመን መሆኑ ታውቋል ። ዳን. ምዕ-12 ቁ.4 ባጠቃላይ ዛሬ በሳይንስ ጥናትና ምርምር የተገኙት ውጤቶች እንደሚያመለክቱት ከታላላቁ ግዑዛን ፍጥረታት አንስቶ ፣ በደመ ነፍስ ሕይወት የሚንቀሳቀሰው ማናቸውም ፍጡር ፣ የተፈጥሮ ባሕርይ እጅግ የሚያስደንቅ ሕግና ሥርዓት ን የሚከተል መሆኑ ፣ በየፈርጁ በተደረጉት ጥናቶች ተደርሶበታል።

ይህንንም የተረዱ የሳይንስ ሊቃውንት ፣ ስነ ፍጥረትን ራሷን የሚመለከትዋት ልክ እንደመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ወይም አገላለጽ አድርገው ነው። ከዚህም የተነሳ በቅዱስ መጽሐፍ የተገለጠው የእግዚአብሐር ቃልና ፣ እያንዳንዱ በስነ ፍጥረት ሰሌዳነት ላይ የሚነበበው የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ፣ ፍጹም ተመሳሳይነት ያለው፣ ወይም አንድ ዓይነት መሆኑን አረጋግጠዋል።

በቅዱሳት መጻሕፍትና በሳይንስ ጥናት ልዩ ልዩ ክፍሎች ያለውን ተመሳሳይነት በሌላም አነጋገር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛነት ሳይንስና የሳይንስ ውጤቶች የሚሰጡትን ምስክርነት ከዚህ ቀጥሎ ባጭሩ ለማሳየት እንሞክራለን።

1. ስለ ዓላማት አፈጣጠር

ሀ መጽሐፍ ቅዱስ፦ « ዓለሞች በእግዚአብሄር ቃል እንደተዘጋጁ ፣ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን » ይላል። ዕብ 11፥3 ይህንንም ግልጽ ለማድረግ በሌላ አነጋገር እንደሚከተለው ለማቅረብ ይቻላል ..... እነሆ ዓላማት በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተፈጠሩ ከማይታየውም ነገር የሚታየው እንደሆነ እናምናለን ።

ለ ፊዚካል ሳይንስ ፦ ማናቸውም ነገር ማተር የተገኘው ፣ ከልዩ ልዩ የንጥረ ባሕርያት ኤለመንትስ ነገሮች ነው። እነዚህም የንጥረ ባሕርያት ነገሮች «አተምስ » ይባላሉ። አቶሞች በፈንታቸው የተቋቋሙት ኤሌክትሮንስ፣ ፕሮቶንስና ኒውትሮንስ ከተባሉ ሌሎች ቅንጣት ነገሮች ነው። የአንዱ ንጥረ ባሕርይ አቶም ከሌላው የንጥረ ባሕርይ አቶም የማይገጥም አንድ ስላይደለ ነገሮች የተቋቋሙባቸው አቶሞች የያንዳንዱ ነገር ዓይነት ወሳኞች ናቸው ከዚህም የተነሳ ወርቅ፣ ወርቅ ቢሆን እንጂ በምንም ዓይነት ብር ወይም መዳብ ሊሆን አይችልም እነዚህ በዓይን አይተን በእጅ የምንዳስሳቸው እንደ ብረት ኒኬል መዳብ ደንጊያ ወርቅ ወዘተ የመሳሰሉ ነገሮች የተቋቋሙባቸው ቅንጣት ነገሮች በደረቅ ዐይንም ሆነ ወይም በማናቸው ልዩ ዘመናዊ መሣርያ አማካይነት ፈጽሞ ሊታዩ የማይችሉ ግን በእርግጥ ያሉ ነገሮች መሆናቸው የታመነ ነው። ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ የዛሬ 1900 ዓመት ገደማ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ «ስለዚህ ይህ የሚታየው ነገር ከሚታዩ ነገሮች እንደሆነ እናምናለን» ያለው ቃል ትክክል መሆኑ፣ እነሆ ዛሬ በሳይንስ ምርምርና ጥናት ሊደርስበት ችሏል ።

2. መሬት በዓየር ላይ የተንጠለጠለች ናት ወይ ?

ሀ መጽሐፍ ቅዱስ ፦

ሰሜንን በባዶ ስፍራ ላይ ይዘረጋል፡ ምድሪቱንም በታችዋ አንዳች አልባ ያንጠለጥላል። « ኢዮብ 26 7። ይላል።

ለ ጂዎግራፊ ያ መሬት አንዳች ነገር ሳይደግፋት በዐየር ላይ በስበት ኃይል ብቻ ፀንታ የቆመች እንጂ አንዳችም ደግፎ የያዛት ነገር አለመኖሩን አረጋግጧል ።

3. መሬት ክብ ናት ዝርግ?

መጽሐፍ ቅዱስ፡ -

ሀ «እርሱ በምድር ክበብ ላይ ይቀመጣል ...» ኢሳ . 40፥ 22። ክበብ የሚለው ቃል በእብራይስጥ ድቡልቡል ክብነት ያለው ማለት መሆኑን የቋንቋ ባለቤቶች አረጋግጠዋል።

ይህም በጂዎግራፊ ትምህርት ስለመሬት ክብነት ከተነገረው ቃል ጋር ፍጹም አንድ ዓይነት መሆኑን ዛሬ የማያውቅ ሰው ያለ አይመስለኝም።

4. ስለ ተሽከርካሪዎች የተነገረ ነገር አለ? መጽሐፍቅዱስ ሠረገሎች (ተሽከርካሪዎች)እንደ እሳት ይንቦገቦጋሉ ... በመንገድ ላይ ይነጉዳሉ ። በአደባባይም ይጋጫሉ። መልካቸው እንደፋና ነው፡ እንደ መብረቅም ይከንፋሉ። ....»ናሆም 2፥3 - 4 ።

እዚህ ላይ በዘመናችን የምናያቸውን የተሽከርካሪዎች ብዛት ፣ የሞዴላቸውን ዓይነትና የፍጥነታቸውን መጠን ፣ በጨለማ ተከታትለው ሲከንፉ የሚታየውን የሚንቦገቦግ ብርሃን በመመልከት ይህ ከክርስቶስ በፊት ፯፻ ዓመት የተነገረው ትንቢት በዘመናችን ደርሶ ሲያዩት ምን ይሰማዎታል ?

XX



# የተፈጥሮ ሕግና የተአምር ለውጥ

ሲማንኛውም ፍጥረት የማያቋርጥ የእድገት እንቅስቃሴ አለው ሕይወት ያለው ሁሉ ይወለዳል ደረጃ በደረጃም የዕድገት ለውጥ እያሳየ ያድጋል ፣ ያረጃል በመጨረሻ ይሞታል ። ይህም የተፈጥሮ ሕግ ለውጥን እንጂ የተአምርን ለውጥ አያሳይም ።

በሌላ በኩል ደግሞ የተፈጥሮ ሕግን ለውጥ የተመለከትን እንደሆነ ውሃ በንጥረ ባሕርዩ አንድ ሆኖ ሳለ በውስጡ ባሉ 3 ባሕርያት (ጠባዮች) ይገለጣል እነርሱም ፦

ሀ/ በጠጣርነት ፣ ለ/ በፈሳሽነት ሐ/ በተንነት

በመጀመሪያ በተገለጠው መሠረት ውሃው ቅርጹ ወደ ጠጣርነት ተለውጦ በረዶ ይሆናል። በረዶውም አስፈላጊውን ሙቀት ሲያገኝ ይቀልጥና ወደ ፈሳሽነት ይለወጣል ። ፈሳሹም ውሃ በከፍተኛ ሙቀት በፈላ ጊዜ ወደ ተንነት ይለወጣል ። ተኑም ሲቀዘቅዝ ተመልሶ ወደ ውሃነት ይለወጣል ። ዞሮ ዞሮ ግን ውኃ እንጂ ሌላ አዲስ ነገር አልተፈጠረም ። ይህ ሁሉ የተፈጥሮ ሕግ እንጂ የተአምር አይደለም ።

መጽሐፍ እንደሚያስተምር ይህንን ሁሉ በመጀመሪያ ጊዜ የወሰነና የደነገገ የተፈጥሮን ሕግ ያቋቋመ አንድ አምላክ አለ ። እሱም ሁሉን የያዘ ሳማይንና ምድርን የሚታየውንና የማይታየውን የፈጠረ ፣ የሥነ ፍጥረት ጌታ እግዚአብሔር ነው ለዚህም መሠረቱ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ የሚለው ቃሉ ነው ኦሪት ዘፍጥረት ምዕ.1 ቁ፥ 1 ።

በተፈጥሮ ሕግ የሚለዋወጡ ነገሮች ከላይ የተጠቀሱት ሲሆኑ ፣ ተአምር ደግሞ በእግዚአብሔር ኃይል የሚፈፀም ስለሆነ ከተፈጥሮ ሕግ በላይ ነው እግዚአብሔር በቅዱሳን ፣ በነቢያት አድሮ ልዩ ልዩ ተአምር ገል ጿል ወደፊትም ይገልፃል።ይኸውም ነቢዩ ሙሴ ሕዝበ እሥራኤልን እየመራ በሚጓዝበት ጊዜ በኅብረተሰቡ ላይ ታላቅ የውኃ ጥም ችግር ደረሰባቸው “ለሦስት ቀንም ያህል እንደተጓዙ ውሃ አላገኙም ነበር ወደ ማራ በደረሱ ጊዜ የማራ ውሃ መራራ ነበርና ሊጠጡት አልቻሉም ሕዝቡም ምን እንጠጣለን ብለው በሙሴ ላይ አንጐራጐሩ ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ጮኸ እግዚአብሔርም እንጨት አሳየው በውሃውም ላይ ጣለው ውሃውም ጣፈጠ ኦሪት ዘፀአት ምዕ.15 ከቁጥ 22 - 25 ይህ ሙሴ በእምነት ፣ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ጮሆና ጸልዮ መራራውን ውሃ ወደ ጣፋጭነት በእግዚአብሔር ቃል ስለለወጠው ተአምር ይባላል ምክንያቱም ብዙሀኑ ሕብረተሰብ በበረሃ ሲጓዝ የሚጠጣው አጥቶ በውሃ ጥም ሲሰቃይ ከችግር ማዳን መስዋዕትነት ስለሆነ ታላቅ ተአምር ሆኖ ተጻፈ ። ኤልሣዕ የትባለውም ነቢይ በጸሎትና በእምነት ታላቅ ተአምር አሳይቷል ይኸውም “የከተማይቱም ሰዎች ኤልሳዕን እነሆ ጌታችን ፣ እንደምታይ የዚች ከተማ ኑሮ መልካም ነው ውሃው ግን ክፉ ነው ምድሪቱም ፍሬዋን ትጨነግፋለች አሉት እርሱም አዲስ ማሰሮ አምጡልኝ ጨውም ጨምሩበት አለ ያንንም አመጡለት ውሃው ወደአለበትም ምንጭ ወጥቶ ጨው ጣለበትና እግዚአብሔር እንዲሁ ይላል ይህን ውሃ ፈውሸዋለሁ ከዚህም በኋላ ሞትና ጭንገፋ አይሆንበትም አለ ኤልሣዕም እንደ ተናገረው ውኃው እስከ ዛሬ ድረስ ተፈውሶአል ።” ይላል 2ተኛ ነገሥት ምዕራፍ 2 ከቁ. 19 - 22

ይህም የሚያመለክተን ኤልሣዕ በጸሎት በእምነት መራራ ሆኖ ይጎዱና ፣ ጤና እየነሳ ያሰቃይ የነበረውን ውሃ በጸሎትና በእምነት በእግዚአብሔር ቃል ለውጦ ከሰማርያ ከተማ ይኖር የነበረውን ኅብረተሰብ ጤናማ እንዲሆን ስላደረገው በእግዚአብሔር ኃይልና ፀጋእየተረጸ ታላቅ ተአምር አሳይቷል። ተአምርም ፣ መንፈሳዊ ለውጥም የሚባለው ይህ ነው ይህ በዘመነ ብሉይ የተፈጸመ ሲሆን ፈፃሚዎቹና ሠራተኞችም የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ ፣ የግብሩ መታወቂያና የሥራው መልክ መሆናቸውን ይገልጽልናል ። በዘመነ ሐዲስም ደግሞ በቃና የተደረገውን ተአምር የተመለከትን እንደሆነ ቃና በገሊላ አውራጃ የምትገኝ የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት አቅራቢያ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያውን ተአምር ያሳየባት የአይሁድ ሕብረተሰብ የሚኖሩባት ትንሽ መንደር ነበረች በዚችው ቃና በተባለች መንደር ክርስቶስ ታላቅ ተአምር አድርጎ አምላክነቱን እንደ ገለጸ ታላቁ መጽሐፍ ይነግረናል ።

ይህንንም ተአምር ብዙ ሰዎች አምነው ተቀብለውታል ዴቪድ ኢዩም የተባለ የስኮትላንድ ተወላጅ ግን “ተአምር የለም ብሏል የሌለበትንም ምክንያት ሲገልጥ ማንኛውም ነገር የተፈጥሮ ሕግን ተከትሎ ስለሚጓዝ ከተፈጥሮ ሕግ በላይ ሥራ መሥራት እንደማይቻል ሲያብራራ ሙሴ መና ከደመና አውርዷል ፣ ውሃ ከድንጋይ አፍልቋል ፣ ክርስቶስም የቃናን ውሃ ወደ ወይን ለውጧል በጠቅላላው ነቢያትም ሆኑ ሐዋርያት ተአምራት ሠሩ ለማለት አንችልም” ሲል ተናግሯል ።

የካንተርበሪው ሊቀ ጳጳስ ቶማስ አኪውይናስ ደግሞ ይህንን በመቃወም ‘.ሁሉን ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር ይቅርና እግዚአብሔር ጥበብን የገለጸላቸው ሊቃውንት የፈለሰፉት ሳይንስ እንኳን ከተፈጥሮ ሕግ በላይ ብዙ አስደናቂ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ነው ። ለምሳሌ ድንጋይ ወደ ሰማይ ብንወረውረው ግራቪቲ ወይንም ስበት መልሶ ያመጣው ነበር በሳይንስ የተሠራው አይሮፕላን ግን ድንጋዩንም ሆነ ማንኛውንም ነገር ወደ ላይ ይዞት ይወጣል ። መርከብ በባሕር ላይ ይንሳፈፋል አንድ ክረጢት አሸዋ ወደ ባሕር ብንወረውረው ግን ባሕሩ ያሰጥመዋል በመርከብ



www.ethiopianorthodox.org

ግን ቢጫን ባሕሩን ይሻገራል በጠቅላላው በእግዚአብሔር ኃይል ተአምራት አይሠሩም ማለት ሳይንስ በየጊዜው የሚገልፃቸውን ሥራዎች ከመወሰን በስተቀር ሌላ ጥቅም የለውም'' ብሏል ። ይህም አባባል ከታላቁ መጽሐፍ ጋር የሚስማማ በመሆኑ ይደገፋል የካንተርበሪው ጳጳስ እንዳለውም

ኤልሣዕ የመረረውን ውሃ ማጣፈጥ ብቻ ሳይሆን የሞተውን ታዳጊ ወጣት ከሞት አስነስቶ ለእናቱ በመስጠቱ ተአምር ሠርቷል 2ተኛ ነገሥት ምዕ. 4 ቁጥር 32 - 37

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ውሃውን ወደ ወይን በመለወጥ ብቻ ሳይወሰን ሙቶ ተቀብሮ አራት ቀን የሆነውን አልዓዛርን ከሞት አስነስቷል ለአይሁድ ሕብረተሰብም ታላቅ ተአምር አሳይቷል ዮሐንስ ምዕ.11ቁ. 39-44

ይህንንም ካየን ወደ ጀመርንበት እንመለስና ክርስቶስ በመጀመሪያ በኃጢአት መሮ የነበረውን ዓለም በጥምቀቱ አጣፈጠ ቀጥሎም ከላይ ወደተጠቀስችው ትንሽ መንደር ሠርግ ተጠርቶ ነበረና ወደዚያ ሄደ ከእናቱና ከደቀመዛሙርቱም ጋር አብሮ ታደመ ድንግል ማርያምም ለሁሉ አዛኝ እንደመሆንዋ መጠን የደጋሾቹ የወይን ጠጅ ተ ጋባዡን ሳያዳርስ ስላለቀባቸው ችግራቸውን እንዲያቃልልላቸው ኢየሱስን ለመነችው ።

እሱም ወደዚህ ዓለም የመጣው ሥራ ለመሥራትና ፣ በቸርነትም ችግረኞችን ለመርዳት ስለሆነ ሊረዳቸው ቅዱስ ፈቃዱ ሆነ ወዲያውም አሳላፊዎቹ እንዲታዘዙት እየቀዱ ውሃውን በየጋኖቹ ሞሉ ከዚያም ኢየሱስ ውሃውን በተአምር ወደ ጠጅ ለውጦ በፊት ከተጠጣው የበለጠ ጣ ፋጭ አደረገው ፣ የተአምራቱን ወይም የምልክቶቹን መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ ክብሩንም ገለጠ የዩሐንስ ወንጌል ምዕ. 2 ከቁ. 1 - 12

ከዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባን አንድ ነገር አለ ክርስቶስ በሠርጉ ቤት ተአምር አድርጎ ውኃውን ወደ ወይን የለወጠው በአንድ ቀን ተጨልጦ የሚያልቀውን ውኃ አልነበረም የሙሽሮቹን ኑሮና የቤተሰቦቹን ሕይወት በጠቅላላው በቃና ዘገሊላ የነበረውን ሕብረተሰብ ጭምር በመንፈስ የለወጠው መሆኑን ነው የሚያስገነዝበን ።

በተጨማሪም ከዚህ የምንማረው ኢየሱስን የምናገኘው በቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ፈቃደኛ ሆነን ከጠራነው በእያንዳንዳችን ቤት ገብቶ እንደሚጎበኘንና የጎደለውንም እንደሚያሟላልን ፣ ያነሰውንም እንደሚያበረክትልን ነው ። ስለዚህ ክርስቶስ ወደ ሠርጋችን ገብቶ እንዲታደም ብንጋብዘውና ሁል ጊዜም በቤታችን ውስጥ እንዲኖር ሥፍራ ብናበጅለት ጋብቻችን የተቀደሰ ከመሆኑም ሌላ መራራ የሆነውን ኑሮአችንን ጣፋጭ እንደሚያደርገው አያጠራጥርም በእኛ ታላቅ ተአምራቱን ያሳያል ክብሩንም ይገልጣልና ።

እንግዲህ ጽሑፋችንን ለማጠቃለል ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ ያደረገው ተአምር በዘመናችን መደገም አለበት ይህም ማለት ቤተ ክርስቲያን ካህናትን አደራጅታና አሰልፋ የትምህርት ዘመቻ ማድረግ በአሁኑ ጊዜ ይፈለግበታል ማለት ነው ።

ይህም ሲባል ውኃውን ወደ ወይን ጠጅነት ለመለወጥ ባይቻልም እንኳ ማይምነትን በትምህርት ፣ ቦዘኔነትን በሥራ ወዳድነት ፣ ጭንጫ የሆነውን መሬት ወደ ልማት በመለወጥ ፣ የውኃ ጉድጓድን እየቆፈሩ ውኃ በማፍለቅ በውኃ ጥም ለሚሰቃየው ሕብረተሰብ ከጥሙ እንዲረካ ማድረግ ነው። በዘመናችን የመንፈስ ለውጥና ታላቅ ተአምራት የሚባለው ይህ በተግባር ሲተረጐም ነው ።

በጠቅላላው በክፋት ፣ በምቀኝነት ፣ በራስ ወዳድነት የመረረውን የሰው ሕይወት በእግዚአብሔር ቃል ፣ በትምህርት እየለወጡ ጣፋጭ ማድረግ ከቤተ ክርስቲያን ይፈለጋል ፣ የሥራም ፣ የመንፈስም ተአምር የሚባለው ትርጉሙ ይህ ነውና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

## ምሥጢረ ቁርባን

ከገጽ ፲ የዞረ

ተለውጦ ሥጋ አምላክና ደመ አምላክ እንደሚሆን ማመን አለብን ማለት ነው ።


እንግዲህ ይህ የምሥጢረ ቁርባን ማስረጃ ጽሑፍ ከረጅም ባጭሩ ከሙሉ በከፊሉ የቀረበ እንጂ በዝርዝር የተገለጠ ባለመሆኑ በተለይ የኢ.ት.ኦ. ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ትምህርተ አበ ነፍስ ወዘተ የተሠኙትን መጻሕፍት በማንበብ ምልእት ስፋቱን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ቁ. መክብብ አጥናው



# ልማት በቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምራ ንዋየ ቅድሳትንና ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ቅርሳ ቅርስ በመሥራት የተለየ ጸጋ አላት በተግባረ እድና በመሳሰሉት ነገሮችም የበለጸገች ናት ።



በጠቅላይ ቤተ ክህነት እየተዘጋጀ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚቀርበው ልብሰ ተክህኖ በዚህ አይነት ነው።

ለምሳሌ በውጭ ሀገር እየተዘጋጁና መልካቸውንም ለወጥ አድርገው ወደ ሀገራችን ገብተው በየመሥሪያ ቤቱ የምንገለገልባቸው የጽሕፈት መሣሪያዎች ከመሰራጨታቸው በፊት በሀገር ውስጥ ከሚገኙ የቀንድ እንስሶች ቆዳቸውን ብራና እያወጣች ቀለምንም ከጋዝ ጥላሸትና ከተለያዩ ቅጠላ ቅጠሎች እየሠራች ፣ ብዕርንም ከመቃና ከአንሥርት ላባ እየቀረጸች በጠቅላላ ከሌሎች ክፍላተ ዓለም አንድንም ነገር ሳትበደር ብራናም ሆነ ቀለም በሀገር ውስጥ ከሚገኙት ምርቶች እየተጠቀመች ሃይማኖትዋን አጽንታ ባህሏንም ጠብቃ መቆየትዋና ይህንን ጥበቧንም ለተከታዩ ትውልድ ማስተላለፏ በኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት ተደርድረው የሚገኙት የብራና መጻሕፍት ምስክሮች ናቸው ።

ይሁን እንጂ ባሁኑም ጊዜ የፊተኛውን ጥበቧን ሳትለቅ በተጨማሪ በመኪና ስፌት ልብሰ ተክህኖውን በልዩ ልዩ ጌጣጌጥ እያስጌጠች በመስፋት በበለጠ ሥራዋን እያካሄደችና እያስፋፋች ናት ።

ለዚሁም የልብሰ ተክህኖ ስፌት እንዴት እንደተጀመረና ማን እንዳቋቋመው የሥራና ጥናት ዕቅድ መምሪያ ኃላፊ የሆኑትን አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስን አነጋግረናቸዋል ።

ትንሣኤ ፦ ይህ የልብሰ ተክህኖ ስፌት ሥራ በስንት ዓ.ም. ተቋቋመ ያቋቋመው ማን ነው ?

አባ ተስፋ ሥላሴ ፦ የልብሰ ተክህኖ የስፌት ሥራ የተቋቋመው በ70 ዓ.ም. ሲሆን የተቋቋመውም በሥራና ዕቅድ መምሪያ ተጠንቶ ከቀረበ በኋላ በቅዱስ ሲኖዶስ መልካም ፈቃድ ነው ።

ትንሣኤ ፦ የልብሰ ተክህኖ ስፌት በቤተ ክህነት ውስጥ መቋቋሙ ይመስገናል ግን በወር ምን ያህል ልብሰ ተክህኖ ሰፍቶ ለሽያጭ ያቀርባል ?

መልስ ፦ ከዚህ በፊት የዚህ የልብሰ ተክህኖ ስፌት ሥራ ሕዝቡ በጣም ስላላወቀውና ሥራውም በሚገባ ስላልተስፋፋ በብዛት ለሽያጭ ማቅረብ አልቻለም ግን በጥቂቱ ከ30 - 35 ያህል ልብሰ ተክህኖ ያቀርብ ነበር ። ዛሬ ግን ሕዝቡ እያወቀው ሥራውም ከፊተኛው ይልቅ እየተሻሻለና እየተስፋፋ በብዛት እየተሸጠ ነው ።

ከ71 - 72 ዓ.ም. ድረስ እንኳን በጥቂቱ ከ390 በላይ ለሚሆኑና ከልብሰ ተክህኖ ተራቁተው ለነበሩ አብያተ ክርስቲያናት አዘጋጅቶ ሙሉ ሙሉ ልብሰ ተክህኖ አከፋፍሏል ፣ በዚህም መሠረት በልብሰ ተክህኖ እጦት የሚመጣው ችግር በቅርብ ጊዜ ከብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንደሚወገድና ልብሰ ተክህኖ የሌላቸው መቅደሶች ከደረሰባቸው ችግር በቀላሉ እንደሚላቀቁ ተስፋችን ጽኑ ነው። ።

ትንሣኤ ፦ ልብሶቹ ከተሰፉ በኋላ ገዥ አጥተው የሚቆዩበት ጊዜ አለ ?

መልስ ፦ ከዚህ ቀደም ብሎ ይሰፋ የነበረው ልብሰ ተክህኖ ከማንም ገቢያ ይገዛ ስለነበርና ነጭ መብሩቅ በመሆኑ የተሰፋው ልብስ በተሎ አይሸጥም ነበር አሁን ግን ለልብሰ ተክህኖ የቤተ ክርስቲያን አርማ ያለበት መስቀልና ሌላም ልዩ ልዩ ጌጣጌጥ ያለበት ሁኖ እንዲሠራ ራስዋ ቤተ ክርስቲያን በእውቅ ስለምታሠራው በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅነት በማግኘቱ ዕለት በዕለት ነው የሚሸጠው ልብሱ ከተሰፋ በኋላ ሳይሸጥ የሚውልበት ጊዜ የለውም ምክንያቱም ይህ የምንሰፋው ልብሰ ተክህኖ ለንግድ ሳይሆን ከልብሰ ተራቁተው ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በመጠነኛ ዋጋ ለማዳረስ ስለሆነ ነው ። ለወደፊትም ቢሆን ምእመናኑ ጥቅሙን አውቀው የቤተ ክርስቲያንንም ችግር ተገንዝበው ችግሩን ለማስወገድ

ወይ. ገጽ ፳፪ ይዞራል



www.ethiopianorthodox.org

# ሊቃውንቶቻችን



ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ ሥላሴ

በኢትዮጵያ ለሥነ ጽሑፍ ስልት ጮራ የሆኑት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በመርሐ ቤቴ አውራጃ ደን አቦ ገዳም በተባለ ቦታ በ1881 ዓ.ም. ተወለዱ የአባታቸው የትውልድ ሀገር ግን አማራ ሳይንት ነው።

ወደ ትምህርት ዓለም የተሠማሩበት ዋና ምክንያት

ደን አቦ ገዳም የተባለውን ቤተ ክርስቲያን ያሠሩት ወይዘሮ ባፌና ፣ አስቀድሞ የአፄ ምኒልክ ባለቤት የነበሩት የብላቴን ጌታ ኅሩይን አባት አቶ ወልደ ሥላሴን የቤተ ርስቱ ኃላፊ ሹም አድርገዋቸው ግብር በሚያበሉበት ወቅት ካህናት የማዕዱን ዙሪያ ከብበው ከተቀመጡ በኋላ የገዳሙ መሪጌታ ባለመምጣቱ አንመገብም ብለው ይጠባበቁ ጀመር ።

አቶ ወልደ ሥላሴ እንዲጋብዙ ቢያስተናብሩ መሪ ጌታው ካልመጣ የማይመገቡ መሆኑን ስለገለጹላቸው ግብዣው ለእሱም በበኩሉ ሊቀርብለት የሚችል መሆኑን ገልጸው እንዲበሉ እንዲጠጡ ስለጠየቁዋቸው ካህናቱ ሲበሉ ወዲያው መሪጌታው ደርሶ እርሱ በሌለበት ምግብ በመጀመራቸው ካህናቱን ክልክ ያለፈ ገሠፃቸው።

አቶ ወልደ ሥላሴ ጭቅጭቁንና ፀቡን ያቀዘቀዙ መስሏቸው ካህናቱ በውጭ፡ በፀሐይ ሙቀት ስለ ተጎዱና ሰነቱ በመተላለፉ እንዲጋበዙ ያደረግሁት እኔ ነኝ እርስዎም ተቀምጠው ይብሉ ይጠጡ» ቢሉት «ግፍ የሚውሉብን ወይዘሮ ባፌና ናቸው አንተ ያልተማርከው ጨዋ ምን ታደርግ ? የተማረ ሰው ተሾሞ ቢሆን ኖሮ መቼ እንዲህ እንደፈር ነበር? አሁንም ከሹመትህ ሳላሽርህ ብቀር ....» ብሎ የማይገባ ቃል ተናገራቸው፣ አቶ ወልደ ሥላሴ ግን ንግግሩን በትዕግሥት ከማዳመጥ በቀር ምንም መልስ አልሰጡም ሆኖም ፀቡ ሳይዘገይ በዕርቅ እንዲበርድ ተደረገ።

አቶ ወልደ ሥላሴ ግን መሪ ጌታው አልተማርክም ብሎ በተናገራቸው ቃል በጣም ተበሳጭተው ነበርና «የእኔ መቸም ቀርቷል እንግዲህ ልጄ እንደእኔ እንዳይሰደብ ማስተማር አለብኝ » የሚል መንፈስ በህሊናቸው አድሮ ለጊዜው በዚያው በገዳሙ የሚገኙት አስተማሪ ልጃቸውን በትጋት እንዲያስተምሩላቸው እየጎተጎቱ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ከዚያው ከተወለዱበት አገር የንባብ ትምህርት ለመከታተል ቻሉ።

አቶ ወልደ ሥላሴ ልጃቸው ወደ ትምህርት ዓለም እንዲያተኩሩ እራሳቸው ባለመማር የደረሳባቸውን ስድብ እያስታወሱ ይመክሩዋቸው ጀመር እንዲያውም ትምህርታቸው በዚያ ገዳም ብቻ ሊጠቃለል የማይቻል መሆኑን እየገለጹ ወደሌላ አገር የሚወስዱዋቸው መሆኑን አረጋግጡላቸው ይሁን እንጂ አሰናካይ ምክንያት እንዳይገጥም በመስጋት ይሆን ውሳኔ ኅሩይ ለወላጅ እናታቸው እንዳይናገሩ አዘውትረው በምክር ያስጠነቅቁዋቸው ነበር።

ብላቴን ጌታ በትምህርት ቤት

አቶ ወልደ ሥላሴ ሹመታቸውን ለወዘሮ ባፌና አስረክበው እንዲሁም ቤታቸውን አደራጅተው ምሥጢሩን ለባለቤታቸው ሳይነግሩ ልጃቸውን ብላቴን ጌታን ይዘው በሌሊት ጉዞዋቸውን ቀጠሉ

ለትምህርት የሚያመችውም በሰላሌ አውራጃ ስሬ የተባለው ቀበሌ መሆኑን ስለአረጋገጡ በጉዞ የደከሙትን ልጃቸውን እየተሸከሙ ከወዳጅ ከዘመድ ቤት እያደሩና እየሰነበቱ ስሬ ከተባለው ቦታ ደርሰው በሻህ ለተባለ የዜማ አስተማሪ አስረከቧቸው።

ብላቴን ጌታ ለአንድ ዓመት ያህል ከዚሁ ትምህርት ቤት ፀዋትወ ዜማ ሲያጠናቀሩ ከቆዩ በኋላ ገብረ ሥላሴ የተባሉ አስተማሪ የመዝገብ ድጓ በቤተልሔም አስመስክረው ከዚያው ስለመጡ ወደ እርሳቸው ተዛውረው የቀራቸውን የዜማ ትምህርት ይልቁንም መዝገብ ድጓ ተምረው ዐወቁ በዚያ ጊዜ የቤተ ልሔም ዜማ ዋናው የያሬድ ዜማ እየተባለ ይጠራ ነበርና እንደብርቅ ይታይ ነበር። ወይዘሮ ፀሐየ ወርቅ ዳርጌ ለአስተማሪያቸውም ሆነ ለእርሳቸው ቀለብ ስለቆረጡላቸው በትምህርት ገበታቸውም ሆነ በልብስ አልተቸገሩም ።

በተጨማሪም ከዚሁ ትምህርት ቤት ጽሕፈትን ለመከታተል ችለዋል አባታቸው ጊዜ ሞታቸው ሲደርስ ልጃቸው በትምህርት እንዲገፉ እንጂ ጉባኤያቸውን ትተው ወደ ትውልድ አገራቸው እንዳይመለሱ የኑዛዜ ቃላቸውን አስተላልፈዋል ።

ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ የጽሕፈት ሥራ እየሠሩ ሳሉ በቾ በተባለ አገር በቅዱስ ጊዮርጊስ በዓል አከባበር ላይ የአዲስ አበባ እንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ሊቃውንት ከነበሩት ከአለቃ ወልደ ሚካኤል፣ ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስና ከአለቃ ዳኜ ጋር ስለተዋወቁ ሊቃውንቱ በሞያቸው ተደስተው ወደ ራጉኤል ደብር ይዘዋቸው መጡ ።

በዚህም ጊዜ የኅሩይ ወልደ ሥላሴ የትምህርትና የዕድል በር ተከፈተ፣ ከተጠቀሱት ሦስት ሊቃውንት መካከል አንደኛውም መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ስማቸውን ቢጠይቋቸው «ገብረ መስቀል እየተባሉ እንደሚጠሩ አስረዱ።

መምህርም እኔ ለትምህርት በጎንደር ሳለሁ አስተማሪዬ ኅሩይ እያሉ ይጠሩኝ ነበር፤ አገሬ ከተመለስኩ በኋላ ግን በቀድሞ ስሜ ወልደ ጊዮርጊስ ተብዬአለሁ ስለዚህ የኔን ስም አበርክቼ ሃለሁና «ኅሩይ» እየተባልክ ተጠራ ስለአሉዋቸው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ገብረ መስቀል የተባለው ስማቸው ቀርቶ «ኅሩይ » ተባሉ ከዚያምበፊት የሆነው ፍሬ እየተባሉ ይጠሩ ነበር። ታዲያ ኅሩይ የሚለው ስም ከዚህ ጋር ይስማማል ።

ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ከቅዱስ ራጉኤል ደብር የቅኔ ትምህርታቸውን ቀጠሉና ልክ በዘጠነኛው ወራቸው ተቀኙ ፤ ከዚህም በኋላ ትምህርት ቀለላቸው እንጎላቸው የምርምር ና የእውቀት ሣጥን ሆነ ቀጥሎም በሦስት ወራት ዕድሜ የቅዳሴ ና የውዳሴ ማርያምን ትርጉም ፡አንድም በሚያሰኘው አወራረድ አጠናቅቀው፡አወቁ፤ የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስ ከዚያው ከእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ደብር የፍትሐ ነገሥትና የቁርሎስን ትርጓሜ በእንጦጦ ማርያም ደብር ከጎንደሩ ሊቅ ከመዝሙር ካሣ በሚገባ አድርገው ተማሩ በዚህም ጊዜ ብ.ጌታና ሊቄገ ክርስቶስ ፍትሐ ነገሥት በአማርኛ ተረጎሙ የብሉያትንም ትርጓሜ ለራሳቸው አጠኑ፣

የቅዱስ ራጉኤል ደብር አስተዳዳሪ የነበሩት ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የኅሩይ ወልደ ሥላሴን የተፈጥሮ ብልህነት የትምህርት አቀባበልና ትጋት በቅርብ ስለተረዱ የተማረና ባለሞያ የሚወዱና የሚያስጠቅሙ ነበሩና ዓይናቸውን ጣሉባቸው፣ ከዚህም የተነሣ ኅሩይ ወልደ ሥላሴን ና አስተማሪያቸውን ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ለዓፄ ምንሊክ አቅርበው አሸለሙዋቸው።

ዓፄ ምኒልክም የአስተማሪያቸውን ተማሪዎች ባዩበት ጊዜ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በዕድሜ ከሁሉ ያነሱ ሆነው ስለተገኙ ይኸንንስ ቁጥር ሟሟያ አቅርበኸው እንደሆነ ነው እንጂ ልጅ ነው ብለው ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴን ስለጠየቅዋቸው «ወአልዐልኩ ኅሩይየ» እንደ ተባለው ዕድሜው እንጂ ትምህርቱ ትንሽ አይደለም ከሁሉም ይበልጣል ብለው መለሱ ።

ኅሩይ ወልደ ሥላሴም ለትምህርቱ ጥርጣሬ ካለ እንጠያየቅ ስለአሉ አፄ ምኒልክ እንዲሁም አብረዋቸው የነበሩት ሁሉ ተሳሳቁ በዚህም ጊዜ ዓፄ ምኒልክ ለአስተማሪያቸው የግምጃ ቀሚስ ድርብና የወርቅ ካፓ እንዲሁም የገንዘብ ሽልማት ሲያደርጉ ለኅሩይ ወልደ ሥላሴም የልብስና የገንዘብ ችሮታ አዘዙላቸው። እቴጌ ጣይቱም ሁኔታውን ሰምተው ለኅሩይ ወልደ ሥላሴ የተለየ ሽልማት ልከውላቸዋል።ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ፣ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ለቅዱስ ራጉኤል በዓል የሰጡትን ቅኔ ሰምተው ስለተደሰቱ ወደ ቤታቸው ወስደው ለበዓሉ ለብሰውት የነበረውን የትከሻቸውን አስደሳች ጃኖ ሸልመዋቸዋል።

የመዓረግና የደረጃ ዕድገት

የተማረን ሊቅ መርዳትና ከከፍተኛ ደረጃ ላይ ለማቆም እንቅልፍ የሌላቸው ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የሊቁ የብላቴን ጌታ ኅሩይ የዕድል መንገድ የሚቀየስበትን ሁኔታ ያወጡ ያወርዱ ጀመር ፤ ባለሥልጣኖች እንዲሁም ዓፄ ምኒልክ በሚገኙበት ቦታ ሁሉ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በትምህርት በትዕግሥትና በፈሊጥ የበሰለ አስተያየት አላቸው እያሉ ማስተዋወቅ ጀመሩ ከዚህ የተነሣ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በመንግሥት ሥራ ከደረጃ ወደ ደረጃ በዕድገት ይዘዋወሩ ጀመር ።

ይልቁንም የውጭ አገር ቋንቋ ትምህርታቸውን በትጋት በመከታተላቸው ባገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ያስገኙትን ዕውቀት ለከፍተኛ ደረጃ ሊያሳጯቸውና ሊያደርሳቸው ስለቻለ የኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለመሆን

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org



# የምእመናን ድምፅ

ይህ አምድ የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን በአስተዳደር ተሐድሶ የምትራመድበትና የምትሻሻልበት ክር ስቲያኖች ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው በቀና መንፈስ አስተያየት የሚያቀርቡበት ነው ። በዚህ ዓምድ ሊቀርቡ የሚገባቸው ጽሑፎች የቤተ ክርስቲያናችን ውሳኔዎች ሳይሆኑ የግለሰቦች አስተያየት መሆናቸውን የዓምዱ ተከታታዮች በቅድሚያ እንዲያውቁልን እንፈልጋለን ።

አዘጋጅ ነቅዓ ጥበብ ወንድም የስልክ ቁጥር 11-66-16 የመልእክት ሣ.ቁ. 3137 አዲስ አበባ

ለምእመናን ድምፅ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከሁሉ በፊት የእግዚአብሔር ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን እያልኩ ምኞቴን እገልጻለሁ ።

በአሁኑ ጊዜ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የሚታየው ጭቅጭቅ በጣም አሳዛኝ ነው ።

እውነተኞች ምእመናን ቤተ ክርስቲያን መጥተው አስቀድሰው ለመሔድ ያስባሉ ግን በሰበካ ጉባኤ የተመረጡት ካህናትና ምእመናን እየተለያዩ አሉቃው አንዱን ወገን እየያዘ ሰላም በመታጣቱ እጅግ በማዘን ላይ ናቸው ።

ምናልባት አንዳንድ ምክር ቢሰጣቸው ከጭቅጭቅና ንትርክ ይመለሱ እንደሆነ ዓላማቸውን እንዲያውቁ ትምህርት አዘል የሆነ ምክርና ተግሣጽ በዓምድህ ላይ እንድትሰጣቸው በትኅትና እጠይቃለሁ ።

አቶ ታምራት ተስፋዬ ከአዲስ አበባ

አቶ ታምራት ተስፋዬ በእውነቱ ያቀረቡት ጥያቄ በአእምሮአችን ሲጉላላ የነበረ የምናየውና የምንሰማው ስለሆነ ጥያቄዎትን መነሻ በማድረግ አንዳንድ አስተያየቶችን ለመጠቆም እንሞክራለን ።

በመሠረቱ በካህናትና በምእመናን የተመረጡት የሰበካ ጉባኤ አባላት ስለአንዲት ቤተ ክርስቲያን እንዲሠሩ መሆኑ ግልጽ ነው ።

እንዲያውም ቃለ አዋዲ፡ም.2 አንቀጽ 6 ከተራ ቁጥር 1-13 ስንመለከት መሥራት የሚገባ ቸውን ያስረዳል ታዲያ በካህናትና በምእመናን በኩል የተመረጡት አባላት የእግዚአብሔር ወንጌለ መንግሥትና የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የሚቃናበትን ትተው ከሌላ ጭቅጭቅ ውስጥ ይገባሉ ።

በተለይ በምእመናን በኩል የተመረጡት የገንዘብ አስተዋጽኦ የሚገኝበትን መንገድ ለመቀየስ የካህናት ኑሮ የሚሻሻልበትን ለመሻት የተመረጡ ነበሩ ታዲያ አንዳንዶች ይህን ዓላማቸውን ዘንግተው የአለቃውን ሥልጣን ነጥቀው ራሳቸው እንዲያዙበትና እንዲናዘዙበት ያደርጋሉ ። በዚህም ምክንያት ፍትሕ ርትዕ አጥተው በእነሱ ጩኸት ከአለቅነታቸው የተባረሩ እንዳሉ ግልጽ ነው

አቶ ታምራት ተስፋዬ እጅግ በጣም የሚያስገርመው ደግሞ በምእመናንና በካህናት ይሠራሉ ተብለው የተመረጡት አባላት ራሳቸው የጭቅጭቅ መድረክ ከፍተው ካህናትንና ምእመናኑን በማለያየት የቤተ ክህነቱን ቅጽረ ግቢ አጣበውት ይታያሉ ።

የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ለማገልገል የተመረጠ ቀርቶ በሥጋዊ አስተዳደርም ቢሆን እውነተኛ ሥራ የማይሠራ ከሆነ ሥራው ራሱ ያጋልጠዋል ለፍርድም ያቀርበዋል ።

ታዲያ ይህን ስንል ሁሉን የሰበካ ጉባዔ አባላት ማለታችን አይደለም ። ብዙዎቹ ዓላማቸውን አውቀው ስለሚሠሩ የእነሱ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ ሰላም ሰፍኖ የካህናቱ ኑሮ ተሻሽሎ የደመወዝ ዕድገት አግኝተው ለሀገር ሰላም ሲጸልዩ ለቤተ ክርስቲያቸው አስተዳደር ዕድገት ሲፋጠኑ ይገኛሉ ።

እነዚህ ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን የቆሙ መሆናቸውን ያመለክታል ። መልካም ምሳሌነታቸውም ለሌሎች አርአያ እንደሚሆን ግልጽ ነው ።

እርስዎ መነሻ አድርገው ያቀረቡት ጥያቄ አስመሳይ የሰበካ ጉባኤ አባላትን የሚመለከት ነው ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኤሊ ለልጆቹ የተናገረውን ቃል እንመልከት "ስለ ክፉ ሥራችሁ ከዚህ ሕዝብ ሁሉ ሰምቻለሁና ስለምን እንዲህ ያለ ነገር ታደርጋላችሁ ? ልጆቼ ሆይ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ኃጢአተኛ በማድረጋችሁ ስለእናንተ የደረሰኝ ወሬ መልካም አይደለምና ይህ አይሆንም ሰውስ ሰውን ቢበድል እግዚአብሔር ይፈርድበታል ሰው ግን እግዚአብሔርን ቢበድል ስለ እርሱ የሚለምን ማን ነው ? እነርሱ ግን እግዚአብሔር ሊገድላቸው ወድዶአልና የአባታቸውን ቃል አልሰሙም (ሳሙ ቀዳ. ም.2ቁጥር 23-26 ።)

አንዳንዶችንም የሰበካ ጉባኤ አባላት ከነዚህ ለይተን እናያቸውም ምክንያቱም የደብሩ አስተዳዳሪና ካህናቱ እያሉ እናንተን ምንአገባችሁ በማለት ውዥምብር ፈጣሪዎች ነገረኞች በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ተሰግስገው ግራ የሚያጋቡ መኖራቸው እየተከሠተ ነውና ነው ።

መቼም ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን የቆሙ የሰበካ ጉባኤ አባላት ሊሠሩ የሚገባቸው ካህናት አገልግሎት እንዲያበረክቱ ምእመናን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ እንጂ የአስተዳደሩን ሥራ ይዘው ጭቅጭቅ የሚፈጥሩ መሆን አይገባቸውም ።

የእግዚአብሔርን ቤት ማስተዳደር የሚችል ሰው ራሱን የገዛ ለሰው ብሎ የማያዳላ ለቤተ ክርስቲያን የቆመ ክርስቶስ ለሰው ብሎ የተቀበለውን ጸዋትወ መከራ የሚያስብ እንጂ የጧፍ ኩስታሪ ያሉቱ ቅዳጅ የሙዳየ ምጽዋት ሳንቲም የሚፈልግ መሆን የለበትም ።

እንግዲህ አቶ ታምራት የሰላም ባለቤት ክርስቶስ "የሚች ልጆች ትሆኑ ዘንድ አልተዋችሁም" እንዳለው እሱን ያመኑ ክርስቲያኖችም በአንዳንድ ጭቅጭቅ ሊርቁት አይገባቸውም ሰላም የሚገኝበትን መንገድ መሻት ንትርክ የሚያስነሡትን ሰዎች ከዚህ አድራጐት እንዲቆጠቡ ማድረግ የእያንዳንዱ ክርስቲያን ኃላፊነት ስለሆነ እርስዎም በበኩልዎ በአካባቢዎ ያሉት ክርስቲያኖች ተስፋ እንዳይቆርጡ እንዲያጽናናቿቸው አደራ እንላለን ።

# አማን በአማን

መንክር ስብሐተ ልደቱ ለመድህን

የሰው ፍቅር ስቦት ሰማያዊ አምላክ
ፍቅሩን ሊያሳየን
ስለ እኛ ሰው ሆነ ከክብሩ ሳይለይ ከላ
ኛው ዙፋን
ጥንት በአዳም ኃጢአት ጨለማ ውጦን
የሰይጣን ማደሪያ ምሽጉ ነበርን
ያለም ልጆች ሁሉ በጨለማ ሳለን
እውነተኛው ብርሃን እነሆ ወጣልን
ሐናና ኢያቄም ሲኖሩ አብረው፣
ይጸልዩ ነበር ልጅ ስጠን ብለው።
በርጅናቸው ወራት ማርያምን አግኝተው
ምሥጋና አቀረቡ ለቸሩ አምላካቸው።
አሳባቸው ሞልቶ በጣም በመደሰት፣
ከፊታቸው ጠፍቶ የኃዘን ምልክት፣
እንደ ስዕለታቸው ጥንቱን እንዳሰቡት
ወደ ቤተ መቅደስ ማርያምን ወሰዷት
ከቤተ መቅደስም ስትኖር በትፍስሕት
መልአኩ እያመጣ ምግቧን ከሰማያት፡
ያጫውቷት ነበር መላእክትም ሌሊት።
እድሜዋ ሲሞላ አሥራ አምስት አመት፡
ለሽማግሌው ዮሴፍ ሰጧት ሊጠብቃት።
ቅዱስ ገብርኤልም እግዚአብሔር ልኮት፣
ድንግል ማርያምን ትጸንሲ አላት።
እሷም ደነገጠች በመላኩ ቃላት፣
እንዲሁም ደጋግሞ መፅነሷን ቢያበሥር፡
ሴቶች እንበለ ወንድ መሬትም ያለ ዘር፡
ለመውለድ አይችሉም ዛሬም ለዘወትር።
ለብሥራቱ ጌታ ይህንኑ ስትል፣
የሚሳነው የለም ለእግዚአብሔር ኃይል
ብሎ መለሰላት ቅዱስ ገብርኤል።
በነዚሁ መልሶች አውቃ መረታቷን፣
የእግዚአብሔር ታምራት የበዛ መሆኑን፣
እነሆ ኝ አመቱ ለእግዚአ ኩሉ ፣
እንደ ቃልህ ይሁን እንደ ቅዱስ ቃሉ።
ጊዜው ደረሰና ትንቢቱ ሲፈጸም፡
ጌታ ተወለደ ውስተ ቤተ ልሔም
የሰው ልጅ በሙሉ ደስ ይበለን አሁን፡
ሊሆን ለእኛ ቤዛ መጥቷልና መድኅን፡
መላእክት ዘመሩ ተሞልተው በጸጋ
አምላክ በጥበቡ ሲወለድ በሥጋ
ስብአ ሰገል ሰምተው የጌታን መወለድ፡
በኮከብ ተመርተው ተጓዙ ለመስገድ።
እጅ መንሻ ወርቅ እጣን ከርቤም አመጡ
ለት፣
ንጉሥ ነህ በማለት ክብሩን ሲገልጹለት
ጽሩይና ንጹሕ ወርቅ አቀረቡለት።
ካህን ነውም ሲሉ ሊቀ ካህናት፣
ጥዑም ሽታ ያለው ዕጣን አመጡለት።
ለሰው ፍቅር ብሎም ስለሚቀምስ ሞት
ከርቤ አቀረቡለት ሊሆነን መድኃኒት።
ሄሮድስም ከነሱ ሰምቶ ልደቱን፣
መላልሶ በቃሉ ጠየቀ ሁሉን።
እነሱም አስረዱት መሆኑን እውነት፣
ያዘው ድንጋጤ እንዲሁም ፍርሃት።
ትንቢቱም ይህ ነበር የተናገሩት፣
አንቺ ቤተ ልሔም የኤፍራታ ምድር፣
ከቶውን አታንሽም ከይሁዳ ሀገር ።
ከአንቺ ይወጣልና ሁሉንም የሚያድን፣
ተብሎ ተነግሮ በነቢያት ጥንቱን ፣
ሄሮድስም ተረዳው ቃለ ትንቢቱን፣
ጠርቶ ጠየቃቸው ሰብአ ሰገልን ።
መጥተው እንዲነግሩት ሲያገኙ ሕፃኑን
ከዚያም ሲመለሱ ተመሩ በእግዜር፣
የሕፃኑ አድራሻ እንዳይነገር ።
ሄሮድስም ተናዶ በጣም ተበሳጭቶ፣
እንዳፌዙበትም በቅርቡ ተረድቶ።
የሁለት ዓመት ሕፃን ከዚያም የሚያንሱ
ትን፣
በሰይፍ አስገደለ አሳረደ ሁሉን ።
በኤርምያስ ትንቢት የተነገረው፣
ጊዜው ተፈጽሞ ደረሰ ይኸው።
ሄሮድስም ሞተና አርኬላዎስ ሲነግሥ ፡
በመልአክ ተመርቶ ዮሴፍም ሲመለስ፡
ቤተ ልሔም ገባ የእስራኤል ንጉሥ፣
ለዓለም መድኅን ሆነ አደገ ክርስቶስ።
ደዌን በመፈወስ ሁሉን በማስተማር፡
ሰይጣንን ድል ነሣው ደባለቀው ካፈር።
ሰዎች ነፃ ወጣን አገኘን ደስታ፣
ተሰቅሎ አዳነን በቅዱስ ጎልጎታ።
ቅዱስ ሥጋውንና ክቡርም ደሙን፡
ዘላለም የማያልፍ ሰጠን ሕይወትን ።
ይበሳጭ ይናደድ ሰይጣን ጠላታችን፡
ኢየሱስ ነውና የሕይወት በራችን።
ከዚህ የበለጠ ምን አለን ደስታ፣
እናቅርብ ምሥጋና ለማያልፈው ጌታ፡

ከወ ት ሀሐይ ሲራክ



www.ethiopianorthodox.org

## ሊቃውንቶቻችን ...

ከገጽ ፲፱ የዞረ

በቁ፣ በዚህም ወቅት ኢትዮጵያ በአዲሱ ሥልጣኔ የምትራመድበት ን ልዩ ልዩ ስልት ማሳየት ጀመሩ ።

ለምሳሌ ያህል ከብዙው በጥቂቱ የተዝካር ድግስ በሚያስከር መጠጥና መላ ቅጥ ባጣ ግብዣ መሆኑ ቀርቶ ለካህናትና ለነዲያን የተወሰነ ገንዘብ በመስጠት እንዲሆን ትምህርት የሰጡ እራሳቸው ናቸው አንድ ባለጉዳይ ይኸይደረግልኝ ብሎ ማመልከቻ ሲያቀርብላቸው ጥያቄውንና አድራሻውን ከነስሙ በማስታወሻቸው ከመዝገቡ በኋላ ጉዳዩ ን ወይም ጥያቄውን አሟልተው ባለጉዳዩን ካለበት ጠርተው የፈለገውን የሚሰጡ የሚያሰጡ እርሳቸው ነበሩ ።

የሠርግንም ድግሥ ለሁለቱ አዲስ ቤት መሥራቾች ወላጆች የጎጆ መውጫ በመስጠት እንዲለውጡት ዕቅዱን ያቀረቡና ሠርተው ያሳዩ እራሳቸው ናቸው፣ ይኸንንም የመሳሰለ ብዙ አሉ።

### ሥነ ጽሑፍ

ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በኢትዮጵያ የድርሰትና የሥነ ጽሑፍ ሥራ ባልተስፋፋበት ዘመን አንጋፋና በር ከፋች ደራሲ ነበሩ፣ እራሳቸው ደርሰው ካሳተሙዋቸው መጻሕፍት ዋናዋናዎቹ1. በኢትዮጵያ የሚገኙ የመጻሕፍት ቁጥ2.ወዳጄ ልቤ፣ 3. ሱካርና ወተት የልጆች ማሳደጊያ 4. ዓዜ ዮሐንስና መተማ 5 የአባት መታሰቢያ ለልጅ ምክር 6. የኢየሩሳሌም መንገድ7.ጎሐ ጽባሕ8.መጽሐፈ ቅኔ 9 የሕይወት ታሪክ በኋላ ዘመን ለሚነሡ ልጆች ማስታወቂያ 10 የአውሮፓ መንገድ መሪና ምክር 11 ደስታና ክብር፣12 ዋዜማ 13 ጥሩ ምንጭ 14 የልቅሶ ዜማ ግጥም 15 ማኅደረ ብርሃን 16 አዲስ ዓለም 17 በዕድሜ መሰንበት 18 የኢትዮጵያ ታሪክ በመባል የሚታወቁ ሲሆኑ ወይዘሮ ጥበብና የሰማይ መንገድ ካርታ የተባሉት ግን ተዘጋጅተው ሳይታተሙ መቆየታቸው ታውቋል።

ድርሰታቸው የበሰለ ጥልቅ ስሜት ያለውና አንባቢን የሚማርክ ነውለምሳሌ «ወዳጄ ልቤ» የተባለው መጽሐፋቸው የሰውን ጠባይና ኑሮ በምሳሌ የሚገልጥ ቅዱሳት መጻሕፍትን በምሥራቅ በምዕራብ በሰሜን በደቡብ እየመሰለ የሚያበረከተው ፍሬ ነገር በጣም የሚመሰገን ነው በአማርኛም በተገለጠው ቅኔያቸው በስተመጨረሻ «እንብላ እንብላ ሲሉ ሰዎች ሥጋ መልከኛው ቢቀር፣ ቆርጠው የሔዱ ብዙ ናቸው እኔን ጨልሞኝ ስደናበር» የሚለውም የሚገኘው በዚሁ በወዳጄ ልቤ መጽሐፋቸው ነው።

አንድ ሺህ አንድ መቶ የሚሆነውን የኢትዮጵያ ሊቃውንት ቅኔ ይዞ እንዲታተም በአደረጉ ትም መጽሐፋቸው የእሳቸው የራሳቸው ቅኔ በብዙ ቦታ ተገልጧል አንዱም ግዕዝ ዐሥረንጉሥ «ኢትዮጵያብነ እግዚእኩሉ ምኒልክሃ ዕንቁ ባሕርይ በቅድመ እህርው ሞት ወመቃብር ሕዙሃን መልክዐ ሠናይ ። ለኩልነ ፀዳለ መንግሥቱ ይትርአይ »» ሲል ይነበባል /አማርኛውም ባጭሩ የሁሉ ጌታ ሆይ ዕንቁ ምኒልክን የመልክ ጎደሎዎች በሆኑ በሞትና መቃብር እርያዎች ፊት አትጣልብን የመንግሥቱ ፀዳል ለሁላችን ይታይ ዘንድ » ማለት ነው።

በጥሩ ምንጭ መጽሐፋቸው ቅዱስ ጴጥሮስ ሦስት ጊዜ መድኃኒታችን ን ስለ መካዱ አስተያየታቸውን ሲገልጹ «ለቅዱስ ጴጥሮስ ፈራ ፣ ዘላበደ ተንቀጠቀጠ ማለት ብቻ ይበቃዋል እንጂ «ካደ» የሚለው ቃል ይከብድበታል» ብለዋል ንዲሁም«ጊዮርጊስ ጸልዮ ጠላቶቹን አቃጠላቸው »ስለሚለው ፣ መድኃኒታችን «ጠላቶቻችሁን ውደዱ » እያለ ማስተማሩን ና በዕለተ ዐርብ ሥቃይ ላፀኑበት አይሁድ » አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁትምና ይቅር በላቸው» ማለቱን እያወቀ ቅዱስ ጊዮርጊስን የሚያህል ሰማዕት ጠላቶቹ በእሳት እንዲቃጠሉ ፈጣሪውን ለመነ ማለት ያስቸግራል ብለው ተችተዋል።

መጻሕፍቶቻቸውንም ሆነ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማሳተም የረዳቸው ያቋቋሙት ጎሐ ጽባሕ ማተሚያ ቤት መሆኑ ታውቋል።

በ1926 ዓ.ም. መንግሥትን አስፈቅደው «ያጥቢያ ኮከብ» የተባለ ጋዜጣ እንዲታተም ማድረጋቸውም ተረጋግጧል ።

እንግዲህ ከዚህ ላይ በጣም የሚያሳዝነው ከላይ እንደተመለከተው ሁሉ የልጃቸውን በትምህርት መሻሻል ተስፋ ያደረጉትና በብርቱ የደከሙት አባታቸው አቶ ወልደ ሥላሴ የልጃቸውን ብላቴን ጌታ ኅሩይ በትምህርትና በሥራ ያገኙትን ዕድገት ሳያዩ ከዚህ ዓለም በሞት መሠወራቸው ነው፣ ሆኖም የልጃቸውም ሆነ የእሳቸው ስም በታሪክ ሕያው ነው።

### ዕረፍት

በ1928 ዓ.ም. ግፈኛው ጠላት ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት የኢትዮጵያ ጉዳይ በጊዜው በነበረው በዓለም ማኅበር ዘንድ ተፋጥኖ ትክክለኛ ፍርድ ባለማግኘቱ በኀዘንና በብስጭት ላይ ሳሉ በስደት በነበሩበት በእንግሊዝ አገር በባዝ ከተማ መስከረም 9 ቀን 1931 ዓ.ም. አርፈው ሥርዓተ ቀብራቸው በክብር ከዚያው ተፈጽሟል የኢትዮጵያ ነፃነት ከተመለሰ በኋላ ግን አስከሬናቸው ከእንግሊዝ አገር መጥቶ ለኢትዮጵያውያን አርበኞች በተዘጋጀው መካነ መቃብር በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ አርፏል ከአለቃ አምደ ፅዮን ተሰማ

1931
1881
50



## ልማት በቤተ ...

ከገጽ ፲፮ የዞረ

ከተባበሩንና ኃይላቸው በሚፈቅድላቸውመጠን ከረዱን ይህየስፌት ሥራ ከዚህ በበለጠ ስለሚስፋፋ ልብሰ ተክህኖ አጥተው በከባድ ችግር ወድቀው ለሚገኙ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት በነጻ የምናደርስበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ለመገምገም እያዳግትም ስለ ሽያጩ ግን አሁንም ቢሆን አስቀድመው በዚህ ዓይነት ስፋልን እያሉ አስቀድመው የሚነግሩንና ለሌላ እንዳይሰጥባቸው አደራ ብለውን የሚሄዱት ከመጠን በላይ ናቸው ።

ትንሣኤ፡- ሥራው ከተቋቋመ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከልብሰ ተክህኖ ሽያጭ የተገኘው ገቢ ምን ያህል ይሆናል?

መልስ ፡-ከልብሱ ሽያጭ የተገኘው ገቢ ምንም እንኳን ከአሰብነው በላይ ቢሆንም እስከ ዛሬ ድረስ የተገኘው ገቢ እንደ ገና መልሰን ልብሶችን ስለምንገዛበት ራሱ በራሱ እየተመላለሰ ነው ያለው ለምሳሌ አንድ መቶ ብር ገቢ ብናደርግ በዚሁ አንፃር ደግሞ አንድ መቶ ብር ወጭ እናደርጋለን ማለት ነው ስለዚህ ሥራው በማደግ ላይ ያለ ሕፃን እንደ መሆኑ መጠን ገንዘቡ ይህን ያህል ካፒታል አለው ለማለት ትንሽ ስለሚያስቸግር ለወደፊት በሰፊው እንገልጸዋለን ።

ትንሣኤ፡- የስፌቱ ሥራ ሲቋቋም የማቋቋሚያ ገንዘብ አልተመደበለትም ወይ?

መልስ፡-ከቅዱስ ሲኖዶስ ታዝዞ ለዚሁ ሥራ ማስኬጃ የሚሆን የተሰጠ ገንዘብ አለ ነገር ግን ለዚሁ ሥራ በቂ ባለ መሆኑና ገንዘቡ የተወሰነ ስለሆነ ሊበቃን ባለ መቻሉ ካገኘነው ገቢ ጨምረን ልብስ እንገዛበታለን።

ትንሣኤ፡-በዚህ ሥራ ተመድበው የሚሠሩት ሠራተኞች ስንት ይሆናሉ እነዚህስ ሠራተኞች ካህናት ናቸው ወይስ ሕዝባውያን ?

መልስ ፡- ለስፌት ሥራ ተመድበው የሚሠሩት ሠራተኞች ለጊዜው አምስት ናቸው ለወደፊት ግን ሥራው እየታየና ሠራተኞችን በብዛት እያሰለጠነ ለመቅጠር ሰፊ ዕቅድ አለው ከዚህ ተመድበው የሚሠሩት ሠራተኞችም ካህናት ናቸው ።

ትንሣኤ ፡- የልብሱን መጠን እየለካ የሚቀደው የት የሰለጠነ ነው ?

መልስ ፡- ልብሱን ለክተውና መጥነው እየቀደዱ ለሰፊዎቹ የሚያቀርቡ ከዚህ የሰለጠኑ ናቸው ።
እኒሁም የልብሰ ተክህኖ ቅድ ባለሞያ መምህር ገብረ እግዚአብሔር ወልደ ሥላሴ ናቸው መምህር ገብረ እግዚአብሔር ወልደ ሥላሴ የሥራን ክቡርነት በሚገባ ስለሚያውቁት ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጋር የልብሰ ተክህኖውን ስፌት በትርፍ ጊዜያቸው በራሳቸው ጥረት ተምረዋል በዚህም ችሎታቸው እነሆ ዛሬ በዚህ ሥራ ተመድበው ለቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ አገልግሎትን እያበረከቱ ናቸው ።

ትንሣኤ ፡- የልብሱን ሽያጭ እየመዘገበ የሚቆጣጠር ሰው አለ ወይስ የተሰፋውን ዝም ብሎ መሸጥ ነው ?

መልስ ፡- የተሰፋውን ልብስ በየዕለቱ እየመዘገበና እየተቆጣጠረ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስም በተከፈተው ባንክ የሚያስገባ ሰው አለ ይህንንም ማለት በጠቅላላ የሚቆጣጠረው በበላይ የቤተ ክህነት ሲሆን ወደ ባንክ የምናስገባው ግን የእኛ የሥራ ፍሬያችን ምን ያህል መሆኑን ለማወቅ ነው ይኸውም አንድ ሰው ከባንክ የሚያስገባ አስፈላጊ ሁኖ በመገኘቱ እነሆ ከሚያዝያ ወር 1972 ዓ.ም. ጀምሮ ማስገባት ጀምሯል ።

ትንሣኤ ፡- ይህ የልብሰ ተክህኖ ሥራ ለወደፊት ያለው ዕቅድ እንዴት ነው?

መልስ ፡- ስለ ሥራው ለወደፊት ያለው ዕቅድ ከውስጥ ካሉት አብያተ ክርስቲያናት ሕብረትንና ግንኙነትን በመፍጠር ሥራውን አስፋፍተን በተቻለን መጠን በኢትዮጵያ ባሉት መላ አብያተ ክርስቲያናት አዳርሰን ሌሎችንም ድኆች አብያተ ክርስቲያናትን ለመርዳት ነው ።

በእውነቱ ከዚህ በፊትም ሆነ ዛሬ ብዙ ስለት የሚገባላቸው አብያተ ክርስቲያናት የወጣውንና የገባውን እያስመዘገበ የሚቆጣጠር ሰው ቢኖርበት ኑሮ በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሁከት ባልተፈጠረም ነበር በቤተ ክርስቲያን የሚገኘውም ገንዘብ ባክኖና የእያንዳንዱ ግለሰብ መበልጸጊያ ሁኖ ባልተገኘም ነበር ።

አሁንም ምርት በሚገኝበት የቤተ ክርስቲያን ድርጅት ሁሉ እግዚአቤሔርን የሚፈራ የቤተ ክርስቲያንንም ትንሣኤ የሚያስብ በየቤተ ክርስቲያኑ ቢኖር መልካም ነውና ያለፈው ቢያልፍ ለወደፊት ይታሰብበት እንላለን ።

ከነፈ ርግብ ማርቆስ



www.ethiopianorthodox.org

## ታቦትና ክብሩ

ከገጽ ፲፩ የዞረ

በመሬታዊው እጅ ተጠመቀ ክርስቶስ ተወለደ ። ክርስቶስ ተጠምቆ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ ወለደን ። በሚልክያስ ትንቢት የተነገረለት የጽድቅ ፀሐይ መውጣቱ መታየቱ እውነት ሆነ የጥምቀቱ ክብር የጥምቀቱ ምሥጢር በእውነት ዕፁብ ድንቅ ነው እያሉ ያመሰግናሉ ። በብሉይ ኪዳን ጽላትና ታቦት በማለት መሀከል ልዩነት የነበረ መሆኑን ቀደም ብለን ገልጸናል ። ይሁን እንጂ በዚያም ጊዜ ቢሆን ዘወትር አጠራሩ የሚጠራው በአጠቃላይ ታቦተ እግዚአብሔር በማለት ነበር ። በሐዲስ ኪዳን ግን ጽላትም ታቦትም አንድ ነው ። ጽላት የእግዚአብሔር ስም የተጻፈበት መሆኑን ታቦት እግዚአብሔር አድሮበት የሚኖር ሕጉ የሚጠበቅበት ኪዳኑ የሚጸናበት አምልኮቱ የሚመሰከርበት መሆኑን ያሳያል ።

እግዚአብሔር አድሮበት የሚኖር በመሆኑ ጸሎት መሥዋዕት ይቀርብበታል ። ኪዳኑ የጸናበት በመሆኑ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሀብተሥጋ ሀብተ ነፍስ ያድልበታል ። አምልኮቱ የሚመሰከርበት በመሆኑ ለእግዚአብሔር የአምልኮት ስግደት እናቀርብበታለን ። ታቦት የሌለበት ማንኛውም ቤት የጸሎት ቤት ቢባል እንጅ ቤተ ክርስቲያን አይባልም።

ስለዚህ ታቦት የሌለበት ቤት ጸሎት ይደረግበታል ትምህርት ይሰጥበታል እንጅ መሥዋዕት አይቀርብበትም ።

አንዳንድ ሰዎች ታቦት በሐዲስ ኪዳን የለም የሚል አስተሳሰብ አላቸው። ልክ አይደለም ቅዱስ ጳውሎስ ሁለተኛ ለቆረንቶስ ሰዎች የጻፈው መልክቱ ጨለማን ከብርሃን የሚያዛምድ ጽድቅን ከኃጢአት የሚያመሳስል ክርስቶስን ከሰይጣን የሚያቀላቅል ምእመናንን ከመናፍቃን የሚያስተካክል ማነው ? ካለ በኋላ የእግዚአብሔርን ታቦት በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማነው ሲል ጽፎአል ። (ግዕዙን ተመልከት ።)

ይህም በሐዲስ ኪዳንም ታቦት በሥራ ላይ መሆኑን ያረጋግጣል ሥራውም መሠዊያነት ነው ። ሥጋው ደሙ ይሰዋበታል ። ሊቃውንትም በሕግ መጽሐፍ (በፍትሐ ነገሥት) ታቦት ከቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት አንዱ መሆኑን አረጋግጠው ያለሱ መሥዋዕት መሠዋት የማይገባ መሆኑን ማንም ሰው ለበዓል ለጸሎት ብሎ ታቦት ማበጀት እቤት ውስጥ ማስቀመጥ የማይገባ መሆኑን ይህን አድርጎ ቢገኝ መንፈሳዊ ቅጣት ሊፈጸምበት የሚገባ መሆኑን ምንጊዜም ታቦት ከመንበሩ መነሣት የማይገባ መሆኑን ሆኖም በበዓል ጊዜ ለዑደት እንደዛሬው አስፈላጊውን ሥርዓት ለመፈጸም በስደት ጊዜ ይዞ ለመሸሽ እንዲቻል የእሳት አደጋ ቢደርስ ለማውጣት እንዲመች ካህናት ሊሸከሙት በሚቻላቸው መጠን ጻሕልና ጽዋ ለማስቀመጥ እንደሚችል ሆኖ እንዲዘጋጅ አዝዘዋል ።

መኖሪያ ቦታውን ማለት መንበሩን በስተ ምሥራቅ በኩል ካለው ግድግዳ ተጠግቶ እንዲሆን ጌታችን በመጽሐፈ ኪዳን አዝዞአል ። በዚህ ምክንያት ታቦት በቤተ ክርስቲያን የምሥጢራተ ሃይማኖት መፈጸሚያ ሆኖ ይኖራል ። ወንጌላዊ ዮሐንስስ እንዲያውም በራእዩ በምዕራፍ 11 ቁጥር 18 “በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ የኪዳኑ ታቦትም ተገለጠ” ሲል በተናገረው ቃል ታቦት ከእኛ ዓለም ውጭም ቦታ ያለው መሆኑንም ያሳየናል ።

እንግዲህ ታቦት የአምላካችን ኃይሉ ክብሩ ቸርነቱ ፍርዱ ጉብኝቱ የሚገለጽበት ስሙ የተጻፈበት ከርሱ ከራሱ የተቀበልነው የሃይማኖት ምልክት ስለሆነ አክብረን ልንጠብቀው ይገባል ።

ታቦቱን የሚሸከሙ ወደ ታቦት የሚቀርቡ ታቦቱን የሚዳስሱ ታቦትን የሚያጥኑ ካህናት ፈጽሞ መጠጥ መጠጣት ሥራቸውን ሳይጨርሱ ታቦቱን ወደ መንበሩ ሳይመልሱ እህል መብላትና ያን እያሸተቱ ወደ ታቦት መቅረብ አገልሎት መፈጸም አይገባቸውም ።

በዚህ ጉዳይ ራሳቸው ካህናትና አለቆች ኃላፊነት ያለባቸው ሁሉ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል ። ያለዚያ በራሳቸውም በሕዝቡም ላይ መቅሠፍት ያመጣሉ ሕዝቡም እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ታቦቱን ሳይነቁ ሳይጠራጠሩ ሳይደፋፈሩ በፍርሀት በሃይማኖት ሆነው ራቅ ብለው ሊያጅቡ ይገባቸዋል ።

እንግዲህ ካህናቱም ሆኑ ሕዝቡ ከዚህ በላይ የገለጥንላቸው የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አውቀው እንደትእዛዙ ቢፈጽሙ ሀብትን በረከትን ያገኛሉ ። ባይፈጽሙ ግን በካህናቱ በናዳብና በአብዩድ በአሮን ልጆች የደረሰው ቅጣት ይደርስባቸዋል ። በሕዝቡም በኦዛ ላይ የታዘዘው መቅሠፍት ይፈጸምባቸዋል።

ኢትዮጵያ በታቦተ እግዚአብሔር ፊት ስትፈጽመው በኖረችው የአምልኮት ሥርዓት ግልጥ ምስክርነት ያለው ሀብትና በረከት ያገኘችበት ተጠብቃ የኖረችበት ስለሆነ የታቦትን ነገር ራሷ ለሌላው ልታስተምር ልትመሰክር የምትችል ናት እንጅ አስተማሪ የምትፈልግ አይደለችም ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን በዚህ በዓል አማካኝነት የሚቀርብልህ መልእክት ይህ ነው ። ልብህን አቅና ሃይማኖትህን አጽና አታመንታ በጎ ምግባርን አበርታ ከአባቶች ያገኘኸውን ባህል አትሀየፍ ለወሬ ለፌዝ አትሸነፍ አምላክህ እግዚአብሔር ያለ የሚኖር ዛሬም ነገም መቸም መች የማይለወጥ ነው ። የሚጠብቅህ አይተኛም አያንቀላፋም ። ምስጋና ለርሱ ይሁን አሜን ።

አለቃ አያሌው ታምሩ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org